# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በጤና ሚኒስቴር

# የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ የማስፈፀሚያ ማንዋል

***ታህሳስ - 2011 ዓ/ም***

**ማውጫ**


1. መቅድም ........ 2
2. መግቢያ ........ 3
3. በሆስፒታሎች የስራ አመራር ቦርድ አፈፃፀም ላይ የሚታዩ ነባራዊ ሁኔታዎች ........ 3
4. ትርጉም ........ 4
5. አላማ ........ 5
6. ፈፃሚ አካላት ........ 5
7. የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ አደረጃጀት ........ 5
    7.1. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የመምረጫ ሒደት ........ 5
    7.2. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የመምረጫ መስፈርት ........ 5
    7.3. የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የሚመረጥበት መስፈርት ........ 5
    7.4. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥርና ስብጥር ........ 6
    7.5. የስራ አመራር ቦርድ አባላት የስራ ዘመን ........ 6
    7.6. የስራ አመራር ቦርድ አባል ከአባልነት የሚገለልባቸዉ ሁኔታዎች ........ 6
8. ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ ........ 7
    8.1. የሥራ አመራር ቦርድ ሃላፊነት እና የስራ ድረሻ ........ 7
    8.2. የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ ........ 8
    8.3. የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ/ስራ አስፈፃሚ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ ........ 9
    8.4. የማህበረሰብ ተወካይ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ ........ 10
    8.5. የሰራተኛ ተወካይ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ ........ 10
    8.6. የሰያሚ አካላት ሃላፊነት እና ተግባር ........ 11
    8.7. የሆስፒታል ሥራ አመራር ቦርድ የመደበኛ ተግባራት አፈፃፀም የመከታተያ መንገዶች ........ 12
9. የሆስፒታል ሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ ስርዓት ........ 13
10. ለቦርድ አባላት የሚከፈል አበል ........ 13
11. የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ ስነ ምግባር ........ 14
12. የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ እና የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ የሥራ ግንኙነት ........ 14
13. የስራ አፈጻጸም ምዘና ........ 15
    13.1. የቦረድ አባላት ምዘና (በጥቅል እና በተናጠል) ........ 15
    13.2. የሆስፒታል ስራ እስኪያጅ ምዘና ........ 15
    13.3. የስራ አመራር ቦረድ ሰያሚ አካላት ምዘና ........ 15
14. የሰያሚ አካላት የስራ አመራር ቦርድ የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት ........ 15
    14.1. ጤና ሚኒስቴር ........ 15

14.2. የክልል ጤና ቢሮዎች/ከተማ አስተዳደር /የዞን/ክፍለ ከተማ ሰያሚ አካላት ........ 16
15. ማጣቀሻዎች /References ........ 16
16. አባሪ፡ ........ 17
አባሪ 1፡ የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ ስራ አፈፃፀም መከታተያ ቸክ ሊስት ........ 1
አባሪ - 2 ፡ የሆስፒታል ቦርድ የጥቅል መመዘኛ ነጥቦች ........ 7
አባሪ- 3 የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ አባለት የግል የመመዘኛ ቅጽ ........ 9
**አባሪ**-4 የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ መመዘኛ ቅጽ (ክፍል-1 ከ 75 %) ........ 11
አባሪ 5፡ የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ መመዘኛ ቅጽ (ክፍል-2 ከ 25 %) ........ 16
አባሪ 6፡ የሆስፒታል ቦርድ የሆስፒታል መልካም አስተዳደር ኢኒዴክስ መለኪያ ቅፅ (Good Governence Index) ........ 18
አባሪ 7፡-የቦርድ ሰያሚ አካላት የሥራ አፈጻጸም መመዘኛ ነጥቦች ........ 20

# *ምስጋና*

*ይህ የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ የማስፈፀሚያ ማኑዋል ከመነሻዉ ጀምሮ የተለያዩ የዝግጅት ሂደቶችን አልፎ ለአገልግሎት እስከሚዉል ድረስ በማስተባበር፣ በሆስፒታሎቻችን የስራ አመራር ቦርድ የስራ አፈፃፀሞች ላይ ያሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን እና ወደፊት የሆስፒታሎችን አገልግሎት ጥራት ለማሻሻል የአመራሩን አቅም በማጎልበት መከናወን ያለባቸዉን የተለያዩ የመነሻ ሃሳቦች እንዲካተቱ በማስቻል በአዉደ ጥናት የላቀ ተሳተፎ ያደረጋችሁ የዝግጅት አስተባባሪ ቡድን አባላት፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፣ የክልል ጤና ቢሮ እና የሆስፒታል ባለሙያዎች፣ አጋር ድርጅቶች እና ሌሎች በአዉደ ጥናት የተሳተፋችሁ ሁሉ በጤና ሚኒስቴር የክሊኒካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ምስጋናዉን ያቀርባል፡፡*

**አስተባባሪ ቡድን**

*ደነቀ አየለ - ጤና ሚኒስቴር - ሰብሳቢ*

*ማህሌት አሳየኸን - ጤና ሚኒሰቴር - አባል*

*ምእራፍ ዋለልኝ - ጤና ሚኒስቴር - አባል*

*ክፍሉ አባ የሮም - ጤና ሚኒስቴር - አባል*

**በአዉደ ጥናት የተሳተፉ አባላት**

*ዶ/ር ዳንኤል ገ/ሚካኤል - ጤና ሚኒስቴር*

*አባስ ሃሰን - ጤና ሚኒስቴር*

*ናኦድ ወንዲራድ - ጤና ሚኒስቴር*

*ሲ/ር ገዛሽኝ ደነቀዉ - ጤና ሚኒስቴር*

*ደነቀ አየለ - ጤና ሚኒስቴር*

*ማህሌት አሳየኸኝ - ጤና ሚኒስቴር*

*ምእራፍ ዋለልኝ - ጤና ሚኒስቴር*

*ማርቆስ ጳዉሎስ - ጤና ሚኒስቴር*

*ክፍሉ አባየሮም - ጤና ሚኒስቴር*

*አብይ ዳዊት - ጤና ሚኒስቴር*

*ሲ/ር ጥሩወርቅ አክሌ - ጤና ሚኒስቴር*

*ያለም ዘዉድ ኢያሌዉ - ጤና ሚኒስቴር*

*ካሱ ቶላ - ጤና ሚኒስቴር*

*ኤርሚያስ ሙላቱ - ጤና ሚኒስቴር*

*መዓዛ ካሳ - ጤና ሚኒስቴር*

*ሴም ዳንኤል - ጤና ሚኒስቴር*

*ሰላማዊት ሰለሞን - ጤና ሚኒስቴር*

*አለዉያ ሙዘይን - ጤና ሚኒስቴር*

*ማርቆስ ኃ/ጊዮርጊስ - አ/አበባ ክ/አስ/ጤ/ጥ/ቢሮ*

*ባዩ ደረሳ - ቤ/ጉ/ጉሙዝ ክ/ጤ/ጥ/ቢሮ*

*ባየህ አጥናፍ - አማራ ክ/ጤ/ጥ/ ቢሮ*

*ያሬድ ሃይሉ - ድሬ ዳዋ ክ/ አስ/ጤ/ጥ/ ቢሮ*

*አብዲ ለገሰ - ኦሮሚያ ክልል ጤ/ጥ/ ቢሮ*

*ሽመልስ አወቀ - አፋር ክልል ጤና ጥ/ ቢሮ*

*ቢኒያም ሽፈራዉ - የደ/ብ/ብ/ህ/ ክ/ጤ/ጥ/ቢሮ*

*ማሂር ሞሃመድ - ሃረሪ ክ/ጤ/ጥ/ቢሮ*

*ትልቁ የሻነዉ - አብት አሶሼት*

*ደረጀ አየለ - ጀፓይጎ ኢትዮጵያ*

*ልዑልሰገድ አበጋዝ - አብት አሶሼት*

*ፀጋየ ንጉሴ - ጀፓይጎ ኢትዮጵያ*

*ዶ/ር ስምረት አምሃ - ጤና ሚኒስቴር*

*ነፃነት ሰጠኝ - ጤና ሚኒስቴር*

*ሲ/ር እታፈራሁ አላማዉ - ጤና ሚኒስቴር*

*ሲ/ር ሲና መርዓዊ - ጤና ሚኒስቴር*

## 1. መቅድም

በጤናዉ ዘርፍ በስራ ላይ ያለዉን አመራር አቅም በማጎልበት የተቋማትን የጤና አገልግሎት ጥራት በማሻሻል የማህበረሰባችንን የጤና ደረጃ ከፍ በማድረግ ጤናማና አምራች ዜጋ እንዲፈጠር ማስቻል የአመራሩን ቁርጠኝነት እና ያላሰለሰ ጥረት የሚጠይቅ ተግባር ነዉ፡፡ በሃገራችን በሚገኙ ሆስፒታሎች በትራንስፎርሜሽን እቀዳችን የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ልዩ ልዩ የጤና አገልግሎት ማሻሻያ ሪፎርሞችን በተሻለ በመፈፀም የተመዘገቡ ለዉጦችንም በተፈጠረዉ የሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ትስስር (EHAQ) እስከታች በማዉረድ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት እና ጥራትን በማሻሻል በርካታ ለዉጦችን ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የስራ አመራር ቦርዱ በተቋሞቻችን ምቹ የስራ ሁኔታዎችን በመፍጠር ሰራተኛዉን በማንቀሳቀስ በሆስፒታሎች ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በማተኮር በባለቤትነት በእቅድ በመምራት፤ በቅርብ በመደገፍ እና በመከታተል በኩል ሰፊ ክፍተት በመኖሩ የተቀመጡ ግቦችን በሚጠበቀዉ ደረጃ ማሳካት አልተቻለም፡፡

በቀሪ የጤና ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የሚጠበቀዉ የሆስፒታሎቻችን የአፈፃፀም ደረጃ ላይ ለመድረስ በርካታ የጋራ ስራዎችን ማከናወን ይጠበቅብናል፡፡ የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድም ከሌሎች አካላት ጋር ያለዉን ትስስር በማጠናከር የሆስፒታሉን ራእይ እና ተልእኮ ሊያሳኩ የሚችሉ ፕሮግራሞችን በመንደፍ የረጅም እና የአጭር ግዜ ግቦችን በማሳካት የሆስፒታሉን የአገልግሎት ጥራት እና ፍትሃዊነት በዘላቂነት የማረጋገጥ ትልቅ ሃላፊነት የተጣለበት አካል ነዉ ። የማህበረሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት የተገልጋዩን ባለቤትነት ማረጋገጥ እና የሚነሱ የማህበረሰብ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ በእቅድ ይዞ አገልግሎቱን ወደ ተሻለ የጥራት ደረጃ ማሸጋገር ይጠበቅበታል፡፡ ስለዚህ የሆስፒታሎችን የስራ አመራር ቦርድ የአመራር እና አስተዳደር አቅም ለማጎልበት ከሚኒስቴር መስሪያቤቱ ጀምሮ ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በጋራ የእቅድ ዝግጅት፤ የድጋፍ እና የእትትል ስርዓት በመዘርጋት ተጠያቂነትን ሊፈጥር በሚችል የአሰራር ማእቀፍ በአዲስ መልክ ወደ ስራ መግባት አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም ይህን የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ የማስፈፀሚያ ማኑዋል በሆስፒታሎችን ተግባራዊ በማድረግ የስራ አመራር ቦርዱ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ በማድረስ የተገልጋዩን ማህበረሰብ ጥራት ያለዉ እና ፍትሃዊ የሆነ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሁላችንም ኃላፊነት መሆኑን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በፅኑ ያምናል፡፡

## 2. መግቢያ

የአገራችን የጤና ፖሊሲ ዋነኛው ትኩረት የአገልግሎት ተደራሽነትን በማረጋገጥ ጥራት እና ፍትሃዊነትን ያረጋገጠ  አገልግሎት በዘላቂነት ማቅረብ ነው፡ይህንንም ለማሳካት አስፈላጊ ከሆኑ መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል የላቀ አመራር ለመፍጠር የሆስፒታል አመራርና አስተዳደርን አቅም በማጎልበት የጤና ክብካቤ የገንዘብ ማግኛ ምንጮችን ማስፋት፤ ከመንግስትና ከሌሎች ምንጮች የተገኘዉን ገንዘብ አጠቃቀም ብቃት ማሳደግና ለህዝብ መሠረታዊ የጤና ፍላጎቶች እንዲዉሉ ማድረግ ዋነኞቹ ናቸው፡ ይሁን እንጂ የሆስፒታሎች ስራ አመራር ቦርድ ቀደም ሲል በትግበራ ላይ የነበሩ አዋጆችን፤ የጤና ክብካቤ ሃብት ማግኛ ስልቶችን እና ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች አገልግሎት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በማስተግበር በሚሰጡት አመራር እና አስተዳደር መሻሻል ያሳዩ ቢሆንም ወጥ የሆነና በዘላቂነት የሆስፒታሎቻቸዉን ግብ ለማሳካት ዋና ዋና ጉዳዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እና ተግባር እየተወጡ እንዳልሆነ በተለያዩ መንገዶች ማየት ተችሏል፡፡

የጤና አገልግሎት ፍትሃዊነት፣ጥራትና በዘላቂነት እንዲረጋገጥ እንዲሁም በጤና አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የህብረተሰቡ የነቃ ተሳትፎ እና የባለቤትነት ስሜት እንዲዳብር ይህንን ከፍተኛ ኃላፊነት  የተሰጠዉ የስራ አመራር ቦርድ አደረጃጀት፤ ግልፅ የሆነ ሀላፊነት እና የስራ ድረሻ በማስቀመጥ በየደረጃዉ ያሉ የሰያሚ አካላትን የድጋፍ እና ክትትል ስርኣት መፍጠር አስፈላጊ ነዉ፡፡

ስለዚህ የሆስፒታሎችን ስራ አመራር ቦርድ የመወሰን ነጻነት፣አቅምና ብቃት በማሳደግ ያልተማከለ የጤና አገልግሎት አመራር እና አስተዳደር ሥርዓትን ለማስፈን እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በድጋፍና ክትትል ተግባር ላይ ሰያሚ አካላት እና ቦርዱ ያላቸዉን ትስስር እና ተሳትፎ የበለጠ ማጎልበትና የተቋማቱ የጤና አገልግሎት ጥራቱን የጠበቁ እንዲሆን፤ በአጠቃላይ የአሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን ወጥ እና ሁሉንም የሆስፒታል ደረጃ ያቀፈ የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ የሚመራበት የማስፈፀሚያ ማኑዋል በአዲስ መልክ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል::

## 3. በሆስፒታሎች የስራ አመራር ቦርድ አፈፃፀም ላይ የሚታዩ ነባራዊ ሁኔታዎች

በሃገራችን የጤና ክብካቤ የሃብት ማግኛ ሪፎርም ስራ ላይ ከዋለበት 19 91 ዓ/ም ጀምሮ በርካታ ሆስፒታሎች በፌደራል እና በክልሎች አዋጅ በስራ አመራር ቦርድ እንዲተዳደሩ በመደረጉ ሆስፒታሎች በሃብት አሰባሰብ እና አጠቃቀም እንዲሁም ባልተማከለ ዉሳኔ አሰጣጥ የተመዘገቡ ለዉጦች ቢኖሩም የመስክ ላይ ጉብኝቶች እና ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት  በሆስፒታሎች የጤና አገልግሎት ጥራት በሚፈለገዉ ደረጃ የህብረተሰቡን ጥያቄ የማይመልስ እና መሻሻል ያለባቸዉ ክፍተቶች እንዳሉ ማየት ይቻላል፡-

- የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ በተሰጠዉ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ ከሆስፒታሉ የሚጠበቁ ግቦችን ለማሳካት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በማተኮር ከመንግስት ከሚመደበዉ በጀት በተጨማሪ አጋር አካላቶችን በማሳተፍ የሃብት ማግኛ ምንጮችን በማስፋት የተገኘዉን ሃብት ለሆስፒታሉ የአገልግሎት ጥራት በማዋል እና በቀጣጥነት ለሆስፒታሎች ድጋፍ በማድረግ
- ከጤና ሚኒስቴር ጀምሮ በየደረጃዉ ያሉ ሰያሚ አካላት በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ የሚደግፉበት ፤ የሚከታተሉበት እና ያለበትን የአፈጻፀም ደረጃ  የሚመዝኑበት እንዲሁም የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ የስራ አመራር ቦርዶች እና ክልል ጤና ቢሮዎች የሚበረታቱበት አሰራር  አለመኖር
- የስራ አመራር ቦርድ አባላት ቦርዱ የተቋቋመበትን ዓላማ እና በሆስፒታል የተሰጣቸዉን የስራ ሃላፊነት በሚገባ ተረድተው ለወከሉት ማህበረሰብ እና ሆስፒታል አገልግሎት መሻሻል በቂ ትኩረት በመስጠት በዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በማተኮር የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት እየተወጡ አለመሆናቸዉ

- በተወሰኑ ሆስፒታሎች የስራ አመራር ቦርድ አባላት ከአንድ ሆስፒታል በላይ በስራ አመራር ቦርድ ሰበሳቢ ወይም በአባልነት ላይ ያሉ በመሆኑ በሃላፊነት መደራረብ ምክንያት የሚጠበቅባቸዉን ለዉጥ እያስመዘገቡ ያለመሆኑ
- በየትኛዉም የሆስፒታል ደረጃ ያለ የስራ አመራር ቦርድ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን በእቅድ ይዞ በመምራት የተቀመጡ ግቦችን በማሳካት ሰፊ ክፍተት መኖሩ
- የስራ አመራር ቦርዱ አጀንዳ ከመደበኛ የስብሰባ ሰዓት በፊት ቀድሞ በግልጽ አለመታወቅና በአጀንዳዉ ላይ ተዘጋጅተዉ አለመቅረብ፤ አጀንዳዎች በሆስፒታሉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ያተኮሩ አለመሆኑ
- ቁልፍ የሆስፒታል የአፈጻጸም አመላካችዎችን በመጠቀም የሆስፒታሎችን የአገልግሎት የጥራት ደረጃ በቀጣይነት አለመገምገም፤ በሚታዩ ክፍተቶች ላይ የማሻሻያ ንድፈ ሃሳብ ያለመቅረፅ
- የብዙ ሆስፒታል ቦርዶች በዙሪያቸዉ ከሚገኙ ከሌሎች ባለድረሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ባህል በሚፈለገዉ ልክ አለመዳበር፤ ቀጣይነት የሌለዉ መሆኑ
- የሆስፒታሎች ቦርድ በሆስፒታሎች የጥምረት ለጥራት ትስስር የእርስ በእርስ የመማማሪያ መድረክ የተገኙ ልምዶች በሆስፒታሉ የደረሱበትን የተግባራዊነት ደረጃ አለመከታተል
- ከተገልጋዩ ህብረተሰብ የሚሰጡትን አሰተያየቶች ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ለአግልግሎት ማሻሻያ እንደ ግብዓት የመጠቀም ልምድ በቀጣይነት አለመሰራቱ
- የአባላት ስብጥር በተወሰኑ ሆስፒታሎች የሰራተኛዉን ወይም የተገልጋዩን ማህበረሰብ ዉክልና ያረጋገጠ አለመሆኑ እና ዉክልና የተሰጣቸዉ አካላትም የወከሉትን ማህበረሰብም ሆነ ሰራተኛ የተመለከቱ ጉዳዮችን በእቅድ ይዞ አለመምራት
- በተወሰኑ ሆስፒታሎች የቦርድ አባላት ዉክልና ከሆስፒታሉ የሚጠበቁ ሃላፊነቶችን ለመወጣት እና የአገልግሎት ጥራት መሻሻል ያላቸዉን የስራ የሃላፊነት ቀረቤታ ያገናዘበ አለመሆኑ
- በብዙ ሆስፒታሎች የቦርድ አባላት በተሰጣቸዉ ሃላፊነት እና ተግባራት ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ተከታታይነት ያለዉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ያለመፈጠሩ.
- ካሁን በፊት በተለያየ ጊዜ ለሆስፒታሎች አገልግሎት ማሻሻያነት በሀገር ደረጃ የወረዱ ሪፎርሞችን በትክክል ተረድተዉ ለወከሉት ሆስፒታል በቂ ድጋፍ እና ክትትል አለማድረግ

  ስለዚህ ይህን መነሻ በመጠቀም የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ ወደተሻለ የአፈፃፀም ደረጃ የሚገባበትን አሰራር በየደረጃዉ መፍጠር አስፈላጊ ነዉ፡፡

## 4. ትርጉም

**የሆስፒታል ሥራ አመራር ቦርድ:** ከተለያዩ አካላት የተዋቀረ አባላት ያሉት በሀገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ሆስፒታሎች የሚሰጠዉን የጤና አገልግሎት በበላይነት የሚመራ ህጋዊ አካል ነዉ፡፡

**ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎች (Key Performance Indicator/KPIs):** *ሆስፒታሎች ከሚሰጡአቸዉ ተግባራት መካከል ዋና ዋና የአገልግሎት ጥራትን ሊያመላክቱ እና ሆስፒታሉን ሊመዝኑ የሚችሉ ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎች ናቸዉ፤*

***የኢትዮጵያ የሆስፒታሎች አገልግሎት ትራንስፎርሜሽን መመሪያ*** (Ethiopia Hospital Service Transformation Guideline **(EHSTG))** ፡ በሆስፒታል የሚሰጠዉ የጤና አገልግሎት አደረጃጀት፤ አመራር እና አስተዳደር ስርአቱን በሁሉም የአገልግሎት ዘርፍ ደረጃዉን የጠበቀ ዉጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆን የሚያስችል የሆስፒታሎች አገልግሎት ማሻሻያ/ማስፈፀሚያ ማኑዋል ነዉ፤

**ሰያሚ አካል** ፡- የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ/ አባላትን ለመሰየም ስልጣን/ዉክልና የተሰጠዉ አካል ነዉ፡፡

## 5. አላማ

በሁሉም የመንግስት ሆስፒታሎች ያለዉ የስራ አመራር ቦርድ የሚመራበት ግልፅ እና ወጥ የሆነ የአሰራር መመሪያ በማዉረድ በየደረጃዉ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሁም ተጠያቂነት የሰፈነበት የጤና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የአመራር እና የአስተዳደር ሥርዓት መፍጠር ነዉ፡፡

## 6. ፈፃሚ አካላት

ይህ የማስፈፀሚያ ማኑዋል በጤናዉ ሴክተር በፌደራል እና በክልል ጤና ቢሮዎች ስር በሚገኙ በሁሉም ደረጃ ባሉ የመንግስት ሆስፒታሎች ከ 2011 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 7. የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ አደረጃጀት

### 7.1. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የመምረጫ ሒደት

የሆስፒታል ቦርድ ከመደራጀቱ በፊት ወይም በነባር ሆስፒታሎች በተለያየ ምክንያት የተጓደሉ አባላትን ማሟላት ሲያስፈልግ የተቀመጡ የአባላት የመምረጫ መስፈርቶችን ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ አባላት ሲመረጡ በጤናዉ ዘርፍ ከሆስፒታሉ ራዕይና ተልዕኮ አንጻር የረጅም እና የአጭር ጊዜ ግቦች ላይ መግባባት መደረስ አለበት፤ ከሚጠበቀዉ ግብ በመነሳት በተግባር ግቡን ሊያስፈፅሙ የሚችሉ አካላትን በእጩነት እንዲቀርቡ ማድረግ እና የጋራ ዉሳኔ ላይ በመድረስ ሰያሚዉ አካል ዉሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ እና አስፈላጊዉን ስልጠና አግኝተዉ ወደስራ እንዲገቡ ያስፈልጋል፡፡

በተመሳሳይ ተገልጋዩን ህብረተሰብ ወይም ሰራተኛዉን ወክልዉ የሚካተቱ አባለት በማህበረሰብ ክንፍ ወይም በሰራተኛዉ ለእጩነት ከተመረጡ በኋላ በቦርዱ ሆስፒታሉ ተጠሪ ለሆነው አካል በደብዳቤ ቀርቦ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ከሚቀጥለዉ መደበኛ ስብሰባ በፊት ዉሳኔ እንዲሰጥበት መደረግ ይኖርበታል፡፡

### 7.2. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የመምረጫ መስፈርት

አባላት ሲመረጡ የሚከተሉትን የመመረጫ መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡

የሆስፒታል ቦርድ አባላትን ለምምረጥ የሚቀመጡ መስፈርቶች እንደ ክልሉ አዋጅ እና መመሪያ የሚለያይ ቢሆንም ባላቸዉ የሃላፊነት ቦታ

ሆስታሉን ለመደገፍ ለጤናዉ ሴክተር ጉልህ አስተዋፆ ሊያበረክቱ የሚችሉ፤ በሆስፒታሉ ቦርድ አባልነት ለማገልገል ሙሉ ፍላጎት ያላቸዉ፤

በሆስፒታሉ አካባቢ የሚኖሩ፤ የተሻለ የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ያላቸው፤ በስራቸው ጠንካራ የሆኑ፤ከሆስፒታሉ እና ከስራ አመራር ቦርዱ የሚጠበቁ ሃላፊነቶች እና የማሻሻያ ሪፎርሞች ላይ በቂ ግንዛቤ ይዘዉ በቦርድ የተያዙ ስትራቴጅክ አቅዶችን እና መደበኛ ተግባራቶችን በእቅድ የመምራት አቅም እና ቁርጠንነት ያላቸው፤በስነ ምግባር የታነፁ እና ከሙስና ተግባር የጸዱ፤ በአጠቃላይ በማህበረሰቡ እና በሰራተኛዉ ተቀባይነት ያገኙ፤ ተገልጋይ እና አገልግሎት ሰጭዉን እንዲሁም አጋር አካላትን በጋራ በማቀናጅት ለጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት መሻሻል በትጋት የሚሰሩ እንዲሆኑ ይጠበቃል።

### 7.3. የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የሚመረጥበት መስፈርት

የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ከስራ አመራር ቦርዱ በሚሰጠዉ አቅጣጫ ከሆስፒታሉ ማኔጅምነት ጋር በጋራ በመሆን ሆስፒታሉ ለሚሰጠዉ የጤና አገልግሎት የተጣለበትን ሃላፊነት በተገቢዉ ለመወጣት ሆስፒታሉን ወክሎ የሚሰራ አካል ነዉ፤ ይህን ሃላፊነት እንዲወጣ ለማስቻል

ስራ አስኪያጅ/ስራ አስፈፃሚ ለሃላፊነት ሲመረጥ ማሟላት ያለበት ዝርዝር ነጥቦች እንደ ክልሉ ነባራዊ ሁኔታ የሚወሰን ቢሆንም መሰረታዊ ነጥቦችን እንዲያሟላ ያስፈልጋል፡፡ አግባብነት ያለው የጤና ሙያ ትምህርት ዝግጅት፤ በአመራርነት የሰራ እና በቂ የስራ ልምድ ያለዉ፤ ከሆስፒታሉ የስራ አመራር ቦርድ ጋር ተቀናጅቶ መስራት የሚችል እና በሰራተኛዉ እና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለዉ እና ድምፅ የተሰጠዉ፤ የስነ ምግባር ጉድለት የሌለበት፤ በነበረበት ሃላፊነት ወይም የስራ ደረጃ የተሻለ ዉጤት ያስመዘገበ፤ በሆስፒታል አገልግሎት እና ልዩ ልዩ ሪፎርሞች ላይ በብቃት የማስፈፀም ልምድ ያለው ሆኖ በእጩነት ከቀረበ በኋላ በሚመለከተው አካል መሰየም ይኖርበታል፡፡

## 7.4. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥርና ስብጥር

የቦርድ አባላትን ለመሰየም እና የአባላት ብዛትን ለመወሰን ሆስፒታሉ ባለበት የፌደራል/የክልል አዋጅ እና ደንቦች መሰረት እንደ ሆስፒታሉ ደረጃ የሚወሰን ቢሆንም የአባላት ምርጫ ሲካሄድ የፆታ፤ የማህበረሰብ እና የሰራተኛ ዉክልና እንዲሁም የሙያ ቀረቤታ እና የስራ ልምድ የመሳሰሉት ከግንዛቤ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡በተጨማሪም አባላት በሆስፒታሉ ሊያበረክቱ የሚችለዉን አስተዋፅዖ ያገናዘበ፣ ከተለያየ የሙያ ዘርፍ የተዉጣጡ እና በጤና አገልግሎቱ የሴቶች እና የህጻናትን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሴቶችን ተሳትፎ ማዕከል ያደረገ የሆስፒታል ቦርድ እንዲፈጠር ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ የቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ከሁለት ሆስፒታል በላይ በሰብሳቢነት ወይም በአባልነት ሊወከል አይችልም፡፡ የቦርድ አባላት ቁጥርን በተመለከተም በክልሎች አዋጅ እና የሆስፒታሎች ደረጃ የሚወስን ቢሆንም ከ 5 - 7 አባላት እንዲኖሩት እና የአባላት ቁጥር መጨመር ሲያስፈልግ እንደ ሆስፒታሉ ነባራዊ ሁኔታ ለሰየመዉ አካል በቦርዱ ጥያቄዉን አቅርቦ ሲወሰንለት ሊጨመር ይችላል፡፡

## 7.5. የስራ አመራር ቦርድ አባላት የስራ ዘመን

የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን በክልል ወይም በፌደራል አዋጅ እና መመሪያ የሚወሰን ቢሆንም አንድ የስራ ዘመን ከ 3 -5 ዓመት ያልበለጠ ሆኖ አንድ የቦርድ አባል በድጋሚ ለሰየመዉ አካል ቀርቦ የአባልነት ዉሳኔ ካገኘ እስከ ሁለት የስራ ዘመን በቦርድ አባልነት መቀጠል ይችላል፡፡ ለሆስፒታሉ ቀጣይነት ያለዉ ለዉጥ የስራ አመራር ቦርዱ በጋራ መግባባት እና ዉሳኔ ለዉጡን በበላይነት እንዲመራ እና እንዲያስቀጥል ትልቅ ሃላፊነት የተሰጠዉ አካል ነዉ፡፡

## 7.6. የስራ አመራር ቦርድ አባል ከአባልነት የሚገለልባቸዉ ሁኔታዎች

አባላት ከላይ በተጠቀሱ ሁኔታዎች በአባልነት እንዲካተቱ በማደረግ የሚጠበቅባቸዉን ሃላፊነት እና የስራ ስርሻ በተገቢዉ መወጣት እንዲችሉ የተመቻቸ የስራ ግንኙነት እና በመተማመን ላ የተመሰረተ የጋራ የቡድን ስራ እንዲፈጠር እና በተስማሙበት የዉል ስምምነት ሰነድ እንዲተዳደሩ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ የቦርድ አባል በሚከተሉት ሁኔታዎች ከአባልነት ሊገለል እና በሌላ ሊተካ ይችላል፡

- በአባልነት ለመቀጠል ፍላጎት ሳያሳይ ሲቀር፤
- በመደበኛ ስብሰባ እለት ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ሁለት ጊዜ እና በላይ የቀረ ከሆነ
- አባሉ/ሏ ከወከለዉ ሆስፒታል ካለበት/ችበት ቦታ እና ሀላፊነት በተለያየ ምክንያት ሲለቅ
- የማህበረሰብ ወይም የሰራተኛ ተወካይ ከሆነ/ች የወከለዉ ማህበረሰብ ወይም ሰራተኛ በአባሉ ላይ እምነት ሲያጣ እና ጥያቄ ሲያቀርብ
- የተሰጠዉን/ጣትን ሃላፊነት እና የስራ ድረሻ በአግባቡ ሳይወጣ/ሳትወጣ ሲቀር/ስትቀር፡
- ከወከለዉ ተቋም ህግ ከሚፈቅድለት ዉጭ በማስረጃ የተረጋገጥ የተገኘ ልዩ ጥቅም ወይም የተፈፀመ የሙስና ተግባር
- ሌሎች ልዩ ልዩ የስነ-ምግባር ችግር ሲያሳይ/ስታሳይ

- በቦርድ ውሳኔ ወቅት የተሰጠን የስራ ድርሻ ያለ በቂ ምክንያት በግድየለሽነት የማይፈጽም ከሆነ … ወዘተ የሚሉት አንድ አባል እንዳይቀጥል የሚያደርጉት ሲሆን እንደሁኔታዉ አባሉ ማስረጃ ወይም ምክንያቱን እንዲያቀርብ ሲያስፈልግ በተጠየቀ በ 15 ቀን ዉስጥ እንዲያቀርብ እና ይህንንም ቦርዱ ገምግሞ የጋራ ውሳኔ የሚያስተላልፍ ከሆነ የቦርዱ ዉሳኔ ሆስፒታሉ ተጠሪ ለሆነዉ አካል ቀርቦ ዉሳኔ እንዲያገኝ ይደረጋል፤ የሚተኩ አባላትንም በእጩነት ሂደቱን ተከትሎ በማቅረብ ከ 1 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከሚቀጥለዉ መደበኛ ስብሰባ በፊት የአባልነት ዉሳኔ እንዲያገኙ/ስያሜ እንዲሰጣቸዉ ይደረጋል፡፡

# 8. ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ

## 8.1. የሥራ አመራር ቦርድ ሃላፊነት እና የስራ ድረሻ

የሆስፒታል ቦርድ በሆስፒታል የመጨረሻው የስልጣን እርከን ደረጃ ሲሆን ተጠሪነቱ ለወከለው/ለሰየመዉ መስሪያ ቤት ይሆናል፡፡ የሚከተሉት ሃላፊነት እና የስራ ድረሻም ይኖሩታል፡

- የሆስፒታሉን ራእይ ፤ ተልእኮ ና ግብ ይቀርጻል፤ ለሆስፒታሉ ሰራተኞች ያስተዋዉቃል፤
- የሆስፒታሉን የረጅም ፤ መካከለኛና ፤ አጭር ጊዜ እቅድ ያወጣል፤ ያፀድቃል፤ለሰራተኛዉ ያሳዉቃል
- የሆስፒታሉ ዓመታዊ የሥራ እቅድ እና በጀት አቅርቦ በሚመለከተዉ አካል ሲጸድቅለት በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል
- ሆስፒታሉን በበላይነት ይመራል፣ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋልይ፤ የአፈፃፀም ምዘና ያካሂዳል፣
- ቦርዱ ሆስፒታሉ እንዲሰበስብ ከተፈቀደለት የውስጥ ገቢ ምንጭ ዉጭ ከሌላ ምንጭ(ማህበረሰብ፤የመንግስት እና የግል ተቋማት፤ አጋር ድርጅቶች) ሃብት የማፈላለግ ስራ በእቅድ ይዞ ይሰራል፤ ይገመግማል፤የተገኘዉ ገቢም ለአገልግሎት ጥራት ማሻሻያ እየዋለ መሆኑን ይከታተላል
- ሆስፒታሉ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የክፍያ ተመን ማሻሻያ ያደርጋል ወይም የዋጋ የማሻሻያ ሃሳብ በመመርመር አስተያየቱን በሰያሚው አካል ለክልሉ ምክር ቤት አስቀርቦ ያስወስናል፤ ሲወሰንም ያስፈፅማል
- የሆስፒታሉን የውስጥ አሰራር መመሪያዎች ያፀድቃል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣
- የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲያስችለው ከሆስፒታሉ የዉስጥ ማኔጅመንት ባሻገር የተለያዩ ኮሚቴዎችን በስሩ ያቋቁማል፣ ሥራቸውንም ይመራል፣የስራ አስኪያጅ እና የሆስፒታሉን አፈፃፀም ይገመግማል
- መክፈል ለሚችሉ ተጠቃሚዎች አማራጭ ለማስፋት፤ ባለሙያዎችንም ለማነቃቃትና ለመያዝ የሚያስችል የግል የሕክምና ክፍል በመንግስት ጤና ተቋማት ውስጥ ለመክፈት የሚቻልበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሆስፒታሉ ተጠንቶ የቀረበለትን ጥናት በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፣
- በማህበረሰቡምሆነ በሰራተኛዉ በሆስፒታሉ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ ተገቢውንም ውሳኔ ይሰጣል፣
- የሆስፒታሉ የሥራ አፈጻጸምና የበጀት ሪፖርት ይገመግማል ዝቅተኛ አፈጻጸሞች እንዲስተካከሉ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡ የአፈጻጸም ሪፖርት በአመት ቢያንስ 4 ጊዜ በጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ገምግሞ ለሰየመው አካል ያቀርባል፡፡
- ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን በኮንትራት ለሶስተኛ ወገን ለመስጠት ሆስፒታሉ አጥንቶ ሢያቀርብ አገልግሎቱ ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥበትን መንገድ ያመቻቻል/ይወስናል፤ የአፈፃፀም ክትትልይዘረጋል
- የሆስፒታሎች አግልሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ሪፎርሞች በአግባቡ መተግበሩን ይከታተላል፤ የተመረጡ የአፈጻጸም አመላካቾች መረጃዎች መሰብሰባቸዉን እና አየተገመገሙ ለሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት በወቅቱ ሪፖርት መደረጋቸዉን ያረጋግጣል፡፡
- በበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎችንና ደንቦችን ተግባራዊነት ይከታተላል፡፡

- ከስራ አስኪያጅ፤ከሰራተኛ ወይም ከተገልጋዩ ማህበረሰብ የሚነሱ ጥያቄዎችን ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል
- በአጠቃላይ የሆስፒታሉ ቦርድ አባላት በጋራም ሆነ በተናጠል የተጣለባቸዉን ሃላፊነትና የስራ ድርሻ በዉጤታማነት መንገድ መወጣት የሚጠበቅባቸዉ በመሆኑ በጋራም ሆነ በተናጠል ለሚወስኗቸዉ ዉሳኔዎች እና በሆስፒታሉ ለሚፈጠሩ ዝቅተኛ አፈፃፀሞች ተጠያቂነት ይኖራቸዋል፡፡ ዉጤታማ የሆነ የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድም የሚከተሉት መሰረታዊ ባህሪያቶች ይኖሩታል፡-
    - ✓ በማንኛዉም የሆስፒታሉ ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች ሙሉ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት የሚወስድ
    - ✓ በሆስፒታሉ እና በተገልጋዩ ማህበረሰብ መካከል ጠንካራ ግንኙነት እና መተማመን እንዲፈጠር ያደርጋል
    - ✓ አሳታፊነት ፤በአገልግሎት ጥራት መጓደል ከተገልጋዩ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጭነት፤
    - ✓ በራስ የመወሰን ብቃት እና በሆስፒታሉ ጉዳዮች ከበላይ አካላት ጋር መልካም ግንኙነት ያለዉ የሚሉት ዋና ዋና ምገለጫዎቹ ናቸዉ፡፡

## 8.2. የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ

የቦርዱ ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ሆስፒታሉ ተጠሪ ለሆነዉ የበላይ አካል/መስሪያ ቤት ኃላፊ ይሆናል፤የሚከተሉትን የሃላፊነት ስራዎችንም ይፈፅማል ያስፈፅማል፡-

- የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርዱን በበላይ ይመራል፤የብርድ ተግባራቶችን ያስተባብራል
- የተሰጠዉን ስልጣን እና ሃላፊነት በተገቢዉ በመረዳት በአግባቡ ስራ ላይ ያዉላል፤ በቦርዱም ሆነ በተለያዩ አካላት ያልተገቡ ተፅእኖዎች በሆስፒታሉ ስራ አስኪያጅ ላይ እንዳይፈፀሙ ክትትል ያደርጋል
- አጠቃላይ ከሆስፒታሉ የሚጠበቁ ተግባራት እና ተልእኮዎችን፤የሆስፒታሉን የአገልግሎት አሰጣጥ እና አሰራር ስርአት፤ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችን በማስተግበር በዋናነት ያስተባብራል፡፡
- የሆስፒታሉ ዉጫዊ እና ዉስጣዊ ተፅእኖዎችን በጥልቀት በመረዳት ችግሮችን ይፈታል፡፡
- የቦርዱን ተግባር ከሆስፒታሉ ተልእኮ ጋር በማስተሳሰር አባላት አቅማቸዉን በመገንባት የላቀ አመራር እና አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡
- ከሆስፒታሉ ስራ አስኪያጅ ጋር እቅድ ይዋዋላል፤የቦርድ ተግባራቶችን ያከፋፍላል፤የሆስፒታል የስትራቴጅክ እና አመታዊ እቅድ ዝግጅት ላይ ይሳተፋል ተፈፃሚነቱንም በቅርበት ይከታተላል፡፡
- የቦርዱን መደበኛ ስብሰባዎች የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ እንዲጸድቅ ያደርጋል፤
- ከሆስፒታሉ ስራ አስኪያጅ ጋር አጀንዳ ይቀርፃል፤አጀንዳ ቀድሞ ያሳዉቃል፤መደበኛ ስብሰባ በጤና መሰጃ አስተዳደር ስርዓት መሰረት ቢያንስ በሩብ ዓመት 1 ጊዜ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ያመቻቻል፤እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባም ይጠራል፤ የሚካሄዱ ስብሰባዎችም ግልጽ አሳታፊ እና በአባላት መካከል የማስፈፀም ተነሳሽነት የተሞላበት ዉይይት እና ዉሳኔ አሰጣጥ ስርአት እንዲፈጠር ያደርጋል፤
- ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ኢጋጥሞት በቦርድ ስብሰባ ላይ መገኘት ካልቻለ ምክትል ሰብሳቢ እንዲሰበስብ ያደርጋል ወይም ከቦርዱ አባላት ዉስጥ በደብዳቤ አንድ ሰዉ ይወክላል ፡፡ ይሁን እንጂ በተከታታ ከሁለት ጊዜ በላይ መወከል አይችልም፡፡ ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ ከቀረ በራሱ ፍላጎት ስራውን እንደለቀቀ ተቆጥሮ በምትኩ ሌላ ሰብሳቢ እንዲተካ ቦረዱ ለሰየመው አካል በሪፖርት ያሳዉቃል፤ ያስወስናል፡
- የሆስፒታሉን የሩብ አመት የስራ አፈፃጸም ሪፖርት ግምገማ ከተደረገ በኋላ ተጠሪ ለሆነዉ አካል በጤና መሰጃ አስተዳደር ስርዓት መሰረት ወቅቱን ጠብቆ መቅረቡን ያደርጋል፤
- የሆስፒታሉ የስራ አፈፃፀም ላይ ችግሮች ሲኖሩም ችግሮችን ለይቶ መፍትሄ ያስቀምጣል፤ እንደ አስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃ ወይም የዉሳኔ ሃሳቦችን ለሰየመዉ መስሪያ ቤት ያቀርባል

- የቦርድ ውሳኔዎችን ተግባራዊነት የከታተላል፤እንዲሁም ለሌሎች አባላት አርዓያ በመሆን እርስ በርስና ከሌሎች አካላት ጋር መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡
- ከስራ አስኪያጅ፤ከሰራተኛ ወይም ከተገልጋዩ ማህበረሰብ የሚነሱ ጥያቄዎችን ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል
- የስራ አስኪያጅ/ስራ አስፈጻሚ ያለበትን የአፈፃፀም ደረጃ ይከታተላል፤ ይመዝናል፤ ድጋፍ ያደርጋል ፤ በተከታታ 2 ጊዜ ዝቅተኛ ዉጤት ካስመዘገበ በቦርድ፤ በሰራተኛዉ እና በማህበረሰቡ አስተችቶ ለሰየመዉ አካል ዉሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፤

## 8.3. የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ/ስራ አስፈፃሚ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ

የሆስፒታ ስራ አስኪያጅ የሆስፒታሉን የእለት ከእለት እንቅስቃሴ በበላይ የሚመራ፤ በስራ አመራር ቦርዱ እና በማኔጅመንቱ መካከል ሆኖ ከሌሎች ሶስተኛ አካላት ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች ሆስፒታሉን የሚወክል፤ ተጠሪነቱ ለሆስፒታሉ ቦርድ/ ሰብሳቢ የሆነ ስልጣን እና ሃላፊነት የተሰጠዉ ነዉ፡፡ የሚከተሉትንም ተግባራት በሃላፊነት ያከናዉናል:

- የሆስፒታሉን አጠቃላይ የአገልግሎት አሰጣጥ እና ማኔጅምንቱን ይመራል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤ የአፈፃፀም ምዘና ያካሂዳል
- ከቦርዱ ጋር በቅርበት በጋራ ይሰራል፤ አስፈላጊውን እገዛም ያደርጋለ፤ መረጃ ይሰጣል
- ከቦርዱ ሰብሳቢ ጋር በመሆን የመደበኛ ስብሰባ አጀንዳ ይቀርፃል፤ቀድሞ ያሳዉቃል
- የሲቪል ሰርቪስ ሕጐችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የሆስፒታሉን ሠራተኞች ቅጥር ከሆስፒታሉ ፍላጎት ጋር የሚሄድ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፣
- የሆስፒታሉን አደረጃጀቶች ይፈጥራል፤ ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት ክትትል በጋራ ይሰራል፣ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ሥራቸውን ይመራል፣ ያስተባብራል፣
- የሆስፒታሉን የረጅም እና የአጭር ጊዜ እቅድ በጋራ አዘጋጅቶ ለቦርድ እና ለሚመለከታቸዉ ያቀርባል፤ሲፀድቅም ስራ ላይ ያዉላል፤ የአፈፃጸም ክትትል ያደርጋል፡፡
- የሆስፒታሉን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በማኔጅመንቱ አስወስኖ ለቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
- ወቅቱን ጠብቆ የሆስፒታሉን የሩብ ዓመት፣ የ 6 ወር እና የዓመት የሥራ ሪፖርት፣ የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ከተገመገመ በኋላ ሆስፒታሉ ተጠሪ ለሆነዉ አካል ይልካል፤
- የዉስጥ እና የዉጭ ኦዲት ዉጤት ማስተካከያዎች መተግበራቸዉን ያረጋግጣል
- የግል ሕክምና ከፍልን ለመክፈት እና ክሊኒካል ያልሆኑ አገልግሎቶችን በኮንትራት ለሶስተኛ ወገን ለመስጥት የአዋጭነት ጥናት እንዲጠና ያደርጋል ፤የቀረበውን ጥናት ለቦርድ አቅርቦ ያጸድቃል፤ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያዉላል
- ቦርዱ እንደሚመራበት አዋጅ እና መመሪያ ሁኔታ በቦርድ አባልነት ወይም ያለድምፅ በአስረጅነት ሊወከል ይችላል
- ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ የውል ስምምነቶች እና ሌሎች የግንኙነት ስራዎች ሆስፒታሉን ይወክላል፣
- የጤና ክብካቤ ሃብት ማግኛ ሪፎርም ትግበራን ንድፈ ሃሳብ ያቀርባል፤የሃብት መንጮችን ይለያል፤ በቦርዱ በተያዘዉ እቅድ ላይ በጋራ ይሰራል፤ ያስፈፅማል
- የቦርድ አባላት በሚሰሩት ስራ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ስልጠናዎችን ያመቻቻል፤
- ከቦርዱ እና ሰብሳቢዉ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፤ከሰያሚ አካላት የሚጠበቁ ዉሳኔዎችን ክትትል ያደርጋል
- በነፃ፤ በዱቤ እና በጤና መድህን ፕሮግራም የሚሰጡ አገልግሎቶችን ፍታሃዊነት ይከታተላል፤የዉል ስምምነት ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል

- ዋና ሥራ አስኪያጅ ለሆስፒታሉ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሆስፒታሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
- የሆስፒታሉ ማኔጅመንት ለቦርድ እንዲቀርቡ የጠየቃቸዉን የዉሳኔ ሃሳቦች በቦርድ ዉሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል
- ማኔጅምነቱን እና የስራ ሂደት መሪዎችን ዉጤት ይመዝናል፤ ይከታተላል፤ ዝቅተኛ ዉጤት ያስመዘገቡ አባላት ካሉ ይደግፋል፤ በመመሪያዉ መሰረት ዉሳኔ ይሰጣል፡፡
- በሆስፒታሉ ላይ በሰራተኛዉ ወይም በተገልጋዩ ማህበረሰብ የሚነሱ ጥያቄዎችን ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል
- የቦርድ አስፈላጊ መረጃዎችን፤ ቃለ ጉባኤዎችን .... ወዘተ ይይዛል

## 8.4. የማህበረሰብ ተወካይ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ

የማህበረሰብ ተወካይ ማለት እንደመንኛዉም የሆስፒታል ቦርድ አባል የተቀመጡ የአባላት መምረጫ መስፈርቶችን የሚያሚላ፤ የሆስፒታሉን ተገልጋይ ማህበረሰብ የሚወክል፤ ዉክልናዉም በማህበረሰቡ ተቀባይነት አግኝቶ በሰያሚዉ አካል ዉሳኔ የተሰጠበት መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚከተሉትንም ዋና ዋና ማህበረሰቡን የተመለከቱ የስራ ሃላፊነቶች መወጣት ይኖርበታል፡

- ✓ እንደማንኛዉም የቦርድ አባል የተሰጡ ሃላፊነቶችን ይፈፅማል፤ያስፈጽማል
- ✓ ተገልጋዩ ማህበረሰብ እና ሆስፒታሉ መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸዉ በጋራ ይሰራል፤ህብረተሰቡ የሚያነሳቸዉን ጉዳዮች በተለያየ የህዝብ መድረክ በመገኘት በሆስፒታል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት እና የተነሱ ክፍተቶችን ከሆስፒታሉ ጋር ማስተካከያ በማድረግ ግብረ መልስ ይሰጣል
- ✓ ከሆስፒታሉ የሚጠበቁ ተግባራትን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ በመያዝ የተለዩ ተግባራትን በእቅድ ይዞ ያስፈጽማል
- ✓ በጤና ክብካቤ ሃብት ማግኛ ሪፎርም አጋር አካላትን (የመንግስት እና የግል ተቋማት፤ በለሃበቶች፤ማህበረሰብ) ድረሻ በመለየት እንዲታቀድ ያደርጋል፤የተገኘዉን ሀብትም ስራ ላይ እንዲዉሉ ከቦርዱ እና ከሆስፒታሉ ማኔጅምነት ጋር ይሰራል፤ክፍተቶችን በጋራ ለማሰተካከል ጥረት ያደርጋል
- ✓ ከተገልጋዩ ማህበረሰብ የሚነሱ ጥያቄዎችን ተፈፃሚነት በቅርብ እየተከታተለ ምላሽ እንዲሰጥበት ያደርጋል
- ✓ ቢያንስ በሩብ አመት አንድ ጊዜ የአጠቃላይ የህዝብ የዉይይት መድረክ እንዲዘጋጅ ያስተባብራል፤ የሚነሱ ጉዳዮች ላይ መግባባት እንዲፈጠር ወይም ክፍተቶች በጋራ የሚስተካከሉበትን መንገድ ይቀይሳል

## 8.5. የሰራተኛ ተወካይ ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ

የሰራተኛ ተወካይ እንደመንኛዉም የሆስፒታል ቦርድ አባል የተቀመጡ የአባላት መምረጫ መስፈርቶችን የሚያሚላ፤ የሆስፒታሉን ሰራተኛ ወክሎ ከመደበኛ ስራዉ ጎን ለጎን ሰራጠኛዉን የተመለከቱ ጉዳይዎችን የሚያስፈፅም አካል ነዉ፡፡ ዉክልናዉም በሰራተኛዉ ተቀባይነት አግኝቶ በሰያሚዉ አካል ዉሳኔ የተሰጠበት መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚከተሉትንም ሰራተኛዉን የተመለከቱ ዋና ዋና የስራ ሃላፊነቶች መወጣት ይኖርበታል፡

- ሰራተኛዉን በተመለከቱ ጉዳይዎች ከሚለከታቸዉ አካላት ጋር በእቅድ ይሰራል
- የሰራተኛ ተወካይ እንደመሆኑ መጠን በሆስፒታሉ እና በሰራተኛዉ መካከል መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ ለሰራተኛዉ ከተቋሙ ሊደረጉ የሚገባቸዉን ተግባራት ያቅዳል፤መፈፀማቸዉን ይከታተላል
- ሰራተኛዉ ሊወጣ የሚገባዉን ሃላፊነት እንዲሁም ማንኛዉንም የሚነሱ አስተዳደራዊ ጉዳይዎች እና የቅሬታ ምንጮችን እየለየ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል
- አጠቃላይ የሰራተኛ ጉዳይዎችን እና ቅሬታዎችን በወቅቱ ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፡፡

- እንደ አስፈላጊነቱ አጠቃላይ የሰራተኛ ስብሰባ እንዲካሄድ እና ሰራተኛዉ የሚያነሳቸዉ ጉዳዮችን ለቦርድ ያቀርባል፤ከቦርዱ ምላሽ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
- በአመት 2 ጊዜ የሰራተኛ የእርካታ ጥናት እንዲካሄድ በጋራ ይሰራል፤ በዉጤቱ ላይም ማሻሻያ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል፡፡

## 8.6. የሰያሚ አካላት ሃላፊነት እና ተግባር

በጤናዉ ሴክተር በየደረጃዉ የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ ሰያሚ አካል በፌደራል እና በክልሎች አዋጅ ሊለያይ ቢችልም የጤና የሚኒስቴር መስሪያ ቤት፤የጤና ቢሮዎችን፤ ከተማ አስተዳደር፤ዞን፤ክፍለከተሞችን ....ወዘተ ያጠቃልላል፡፡

**በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ደረጃ፡**

- የክልል ጤና ቢሮዎች/ከተማ ስተዳደር ከሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ ጋር ማስፈጸም የሚችልበት የዉል ስምምነት/ የጋራ እቅድ መዘጋጀቱን ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
- በቀጥታ ከሚሰይማቸዉ የሆስፒታል ቦርድ ጋር በጋራ ያቅዳል/የዉል ስምምነት ይፈራረማል
- የክልል ጤና ቢሮዎች/ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎችን ከሆስፒታል ቦርዶች ጋር ያላቸዉን የስራ አፈጻፀም ቢያነስ በዐመት 2 ጊዜ ድጋፍ እና ክትትል እንዲሁም የጋራ ግምገማ እና ምዘና ያደርጋልምዘና
- የሰየማቸዉን የሆስፒታል ቦርዶች ቢያንስ በአመት 2 ጊዜ አጠቃላይ ስራዎች አስመልከቶ ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋሉ፤ ግብረ መልስ ይሰጣል፤
- ጥቅል የሆስፒታል ቦርድ አፈፃፀም በአመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ በክልል ቢሮዎች እና ሆስፒታሎች ጋር በጋራ ይገመግማል፤ የማሻሻያ ሃሳቦችን ያስቀምጣል፤የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤
- በሰየማቸዉ የሆስፒታል ቦርድ ስብሰባ ከተቀመጠዉ ጊዜ ተራዝሞ ወይም የመደበኛ ስብሰባ በተከታታይ ሁለት ጊዜ ከተቋረጠ ሪፖርት ሲቀርብለት ወቅታዊ የማስተካከያ ዉሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡
- በቦርዱ አፈፃፀም የሚታዩ ክፍተቶች ካሉ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመሆን የድጋፍ መርሃ ግብር በመዉጣት አስፈላጊዉነን ድጋፍ ያደርጋል፤ የሚቀመጡ የማስተካከያ አማራጮች እንደተጠበቁ ሆኖ በተከታታይ 2 ጊዜ ዝቅተኛ ዉጤት ያስመዘገበ ስራ አመራር ቦርድ ወይም አባል ካለ የተሰጠዉን ሃላፊነት እንዳልተወጣ ተቆጥሮ ቦርዱ በአዲስ እንዲቋቋም/ከአባልነት እንዲነሳ ያደርጋል፡፡
- ከቦርድ የሚቀርቡ ዉሳኔ የሚፈልጉ እና ሌሎች ጥያቄዎች ላይ ወቅታዊ ዉሳኔ ይሰጣል
- ጥሩ አፈፃፀም ላስመዘገቡ የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርዶች እና ክልሎች የማበረታቻ ፕሮግራም ያወጣል፤እውቅና ይሰጣል፡፡

**በክልል ጤና ቢሮ/ ከተማ አስተዳደር/ዞን/ክፍለከተማ ደረጃ፡**

- የቦርድ አባላትን እንደ ክልሉ አዋጅ እና መመሪያ ሁኔታ ሊሰይም ይችላል፤ በተዘጋጀዉ ማኑዋል መሰረት ቦርድ መቋቋሙን እና በስራ ላይ መሆኑን ክትትል ያደረጋል
- ከሆስፒታሎች ቦርድ ጋር የዉል ስምምነት መፈፀም/የጋራ እቅድ ማቀደቅ ይኖርበታል
- የሆስፒታል ቦርድ የስብሰባ ስርዓት በክልሉ አዋጅ እና በመመሪያዉ መሰረት የማይፈፀም ከሆነ እና የቦርድ ሰብሰባ ከተቀመጠዉ ጊዜ ተራዝሞ ወይም በተከታታይ ሁለት የመደበኛ ስብሰባ ጊዜ ከተቋረጠ ሪፖርት ሲቀርብለት ወቅታዊ ዉሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፤
- በአመት ሁለት ጊዜ የስራ አመራር ቦርዱ ያለበት የስራ አፈፃፀም ላይ ድጋፋዊ ጉብኝት ያደርጋል
- የቦርዱን አፈፃፀም በአመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ በጋራ ይገመግማል፤

- በቦርዱ አፈፃፀም የሚታዩ ክፍተቶች ካሉ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመሆን የድጋፍ መርሃ ግብር በመዉጣት አስፈላጊዉነን ድጋፍ ያደርጋል፤ የሚቀመጡ ማስተካከያ አማራጮች እንደተጠበቁ ሆኖ በተከታታይ 2 ጊዜ ዝቅተኛ ዉጤት ያስመዘገበ ስራ አመራር ቦርድ ካለ የተሰጠዉን ሃላፊነት እንዳልተወጣ ተቆጥሮ ቦርዱ በአዲስ እንዲቋቋም/አባላት እንዲቀየሩ ያደርጋል፡፡
- ከቦርድ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ላይ ወቅታዊ ዉሳኔ ይሰጣል
- ጥሩ አፈፃፀም ላስመዘገቡ የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርዶች እውቅና ይሰጣል፡፡

## 8.7. የሆስፒታል ሥራ አመራር ቦርድ የመደበኛ ተግባራት አፈፃፀም የመከታተያ መንገዶች

የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት በተሰጠዉ ስልጣን እና ተግባር መሰረት የመከታተያ ስልቶችን በመንደፍ ያከናዉናል፤ ግበረ መልስ ይሰጣል፡፡ የሆስፒታሉን የስራ አፈጻጸም ለመከታተልና ለመገምገም የሚጠቀምባቸው  ስልቶችም የሚከተሉት ናቸው፡-

**የአገልግሎት ክፍሎች ላይ የሥራ ላይ ጉብኝት ማካሄድ፡**

በሆስፒታሉ ዉስጥ ያሉትን ሁለንተናዊ ተግባራትና እንቅስቃሴዎች ግልጽ የሆነ የጊዜ ሰሌዳ በማዉጣት በአካል በመገኘት *በአባሪ 1* የተመለከተውን የመከታተያ ቅፅ በመጠቀም ቢያንስ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ ከመደበኛ ስብሰባዉ በፊት በቂ ግዜ ሰጥቶ ድጋፋዊ ጉብኝት ያደርጋል፤ በግኝቱ ላይም ለስራ ክፍሎችም ሆነ ለሆስፒታሉ ግብረ መልስ ይሰጣል፡ የስራ አመራር ቦርዱ

**የስራ አመራር ቦርድ መደበኛ ስብሰባ ማካሄድ፡**

የክልሉ አዋጅ በሚፈቅደዉ መነሻ መሰረት በእቅድ በተቀመጠዉ የሰብሰባ ጊዜ ሰሌዳ መሠረት መመራት አለበት፡፡ የተያዘዉ የስብሰባ የጊዜ ሰሌዳ በታቀደዉ መሰረት እንዲፈጸም የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፤ አባላቱም ተወያይተዉ እንዲያፀድቁት ያደረጋል፡፡ የመደበኛ ስብሰባዉም የማህበረሰብ እና የሰራተኛ ዉይይት፤ የስራ ላይ ጉብኝት ከተደረገ በኋላ መካሄድ ይኖርበታል፡፡

**በስብሰባ ወቅት ቦርዱ ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ቋሚ የመወያያ አጀንዳዎች፡**

***ሀ***/ የሃብት ማግኛ ስልቶች የእቅድ አፈፃፀም እና የሆስፒታል አገልግሎት ትራንስፎርሜሽን ማኑዋል አተገባበር ያለበትን ደረጃ መገምገም

***ለ***/ የተመረጡ የቁልፍ አፈጻጸም መለኪያዎችን (KPI) መገምገም

***ሐ***/ *በአባሪ 6* በተመለከተው መሰረት የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ መመዘኛ ካርድ በመጠቀም የሆስፒታሉን አገልግሎት አሰጣጥ መመዘን እና ግብረ መልስ መስጠት

***መ***/ የጤና ክብካቤ የሃብት ማግኛ ሪፎርም ተግባራዊ በማድረግ የዉስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን ከእቅድ አንፃር መገምገም እና የመፍትሄ ሃሳብ ማስቀመጥ

***ሠ***/ የጤና ተቋሙን ሲኒየር ማኔጅመንት ቲም እና ቦርዱ ያደረጉትን የስራ ላይ ምልከታ  ውጤት መገምገም፤ የማስተካከያ አቅጣጫ ማስቀመጥ እና መከታተል፡፡

***ረ***/ የሆስፒታሉን HSTQ/Clinical audit ዉጤት ያለበትን ደረጃ እና በተገኘዉ ዉጤት ላይ የተለያዩ የጥራት ማማሻሻያ ፕሮጀክቶች አተገባበር ያለበትን ደረጃ መገምገም

***ሰ***/ ሌሎች አጀንዳዎች እንዳስፈላጊነቱ ሊቀረፁ ይችላሉ፡፡

**የሆስፒታል ጠቅላላ ሠራተኛ ስብሰባ ማካሄድ፡**

ግልፅ የሆነ የስብሰባ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ምቹ እና የስራ ተነሳሽነትን ሊፈጥር የሚችልተቋም እንዲፈጠር የሰራተኛዉ እና የሆስፒታሉ ግንኙነት የሚጠናከርበትን መንገድ በእቅድ በመያዝ የተከናወኑ ተግባራቶችን፤ የሰራተኛ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ዉጤቶችን .... ወዘተ ያቀርባል፤የስወስናል

ሰራተኛዉ የሚያነሳቸዉን ጉዳይዎች፤የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ ውጤት እና የስራ አመራር ቦርድ የሆስፒታል መከታተያ ቅፅ በመጠቀም ያካሄደውን የሆስፒታል ጉብኝት (Facility walk through) መሰረት በማድረግ በየሶስት ወር አንድ ጊዜ የሆስፒታል ሠራተኛ ያወያያል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ግብረ መልስ ይሰጣል፤

ቀድመዉ የተነሱ ጉዳይዎችን ለመፍታት የተደረሰበትን ዉጤት ለሰራተኛዉ ግብረመልስ ይሰጣል

**ከተገልጋዩ ማህበረሰብ፤ከሌሎች ሴክተር መስሪያቤቶችና አጋሮች ጋር ዉይይት ማድረግ፡**

ከተገልጋዩ ማህበረሰብ፤ከሚመለከታቸዉ አጋር አካላትና ሴክተር መስሪያቤቶች ጋር ቢያንስ በ 6 ወር ወር አንድ ጊዜ ተገናኝቶ በዋና ዋና የሆስፒታሉ አፈፃፀሞች ላይ ከእቅድ አንፃር የተከናዉኑ ተግባራት ላይ ዉይይት ያደረጋል፡፡ ይህን መድረክ በመጠቀም የሆስፒታሉን ቁልፍ ችግሮችን ለመፍታት (የውሃ፤የመብራት፤የመንገድ፤የግንባታን)፤ የውስጥ ገቢን ለማሳደግ፤እና በአፈፃፀም ክፍተቶች ላይ ከህብረተሰቡ የተሰጡትን አስተያየት በግብአትነት በመዉሰድ ለአገልግሎት መሻሻል የተቀናጀ አሰራርን በጋራ ለመፍጠር ይጠቀምበታል፤ ግብረ መልስ ይሰጣል

**የልምድ ልዉዉጥ ማካሄድ፡**

በሆስፒታሎች የክላስተር ዉይይት ወይም የተሻለ ልምድ ካላቸዉ ሆስፒታሎች በመገኘት ከስራ አመራር ቦርዱ ጋር በመገናኛት የልምድ ልውውጥ ያከናውናል፡፡ በዚህ ልምድ ልውውጥ የስራ አመራር ቦርዶች በጋራ የስራ ክንውናቸውን የሚገመግሙበት፤ የተሻለ የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድ የአሰራር ልምድ የሚያካፈሉበት፤ተሳታፊዎቹም ልምዱን ወስደዉ ወደተግባር የሚቀይሩበት ይሆናል፡፡

## 9. የሆስፒታል ሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ ስርዓት

ለዉሳኔ እና ግብረ መልስ አሰጣጥ መጠናከር ከቦርዱ የመደበኛ ስብሰባ በፊት የማህበረሰብ ዉይይት፤የሰራተኛ ዉይይት፤ የስራ ላይ ጉብኝቶች ቀድሚያ እንዲካሄዱ ያስፈልጋል

የስራ አመራር ሰብሳቢ እና ስራ አስከያጅ በጋራ የቦርዱን የመወያያ አጀንዳዎች ቀርፀው ከስብሰባው 3-7 ቀን በፊት ለአባላት እንዲደርሳቸው ያደርጋሉ፡፡

መደበኛ ስብሰባ ለማካሄድ የስብሰባ ምልዓተ ጉባዔ ሲሟላ (ከአባላት መካከል ግማሽ እና በላይ) የሚሆኑት ሲገኙ ብቻ ነው፤

ሁሉም አባላት በስብሰባ ላይ መገኘትና የነቃ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው፤

ውሳኔ የሚሰጠው በአብላጫ ድምፅ (50% + 1) ሆኖ የአባላት ዉሳኔ ሁለት እኩል የተከፈለ የዉሳኔ ድምፅ ላይ ከተደረሰ ሰብሳቢው የሚደግፈው ሃሳብ ተፈፃሚ ይሆናል፤

ሁሉም አባላት በጋራ ላፀደቁት የስብሰባ የጊዜ ሰሌዳ፤የመግባቢያ ሰነድ፤የጋራ ዉሳኔዎች ተግባራዊነት ተገዢ መሆን አለባቸው፤

ሁሉም የቦርዱ ስብሰባዎችና ዉሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ የተደገፉ ይሆናሉ፤ አስፈላጊ ተያያዥ ክፍያዎችም እንዲፈፀሙ ይደረጋል

## 10. ለቦርድ አባላት የሚከፈል አበል

የስራ አመራር ቦርድ የአበል ክፍያ በፌደራል እና በክልል አዋጅ እንዲሁም በሆስፒታሎች ደረጃ የሚወሰን ሊሆን ይችላል፡፡ ክፍያዉም የተጠቀሱ ቅድም ሁኔታዎችን ላሟሉ በእለቱ ለተገኙ ተሳታፊ አባላትብቻ ይሆናል፡፡

**ለአበል ክፍያ ተፈፃሚነት መሟላት ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች፡**

የቦርድ አባላት ክፍያ ተፈፃሚ የሚሆነው ቦርዱ በቡድንም ሆነ በተናጠል የሚሰጠውን ተግባር ለተወጣ የቦርድ አባል ይሆናል፤ ለዚህም የቦርድ ሰብሳቢ የመከታተልና የመቆጣጠር ሀላፊነት ይኖርበታል፡

ክፍያው የሚፈፀመው በመደበኛ ስብሰባ ለተገኙ አባላት ብቻ ይሆናል፡

ስብሰባ ባልተካሄደበት ወቅት እንዲሁም ከመደበኛ የስብሰባ ጊዜ ዉጭ ለሚደረግ አስቸኳይ ስብሰባ የአበል ክፍያ አይፈፀምም፡፡

አበሉ እንዲከፈል በእለቱ የተገኙ ተሳታፊዎችን ዝርዝር በፁሑፍ የቦርዱ ሰብሳቢዉ ለሆስፒታሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ማሳወቅ እና የሆስፒታሉ ፋይናንስ እንዲከፍል የሆስፒታሉ ስራ አስኪያጅ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ የአበል ክፍያዉም ከመንግስት በጀት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## 11. የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ ስነ ምግባር

**ከላይ በአባላት የመምረጫ መስፈርት የተቀመጡ ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆኖ አባላት በስራ ላይ በሚያሳልፉበት ጊዜ  የሚከተሉትን መፈፀም ይኖርባቸዋል፡**

- ሁሉም አባላት ላወጡት ደንብ በመገዛት የስብሰባ ህግን በማክበር በመደበኛ የቦርዱ ስብሰባ ላይ በሰዓቱ መገኘት አለባችው
- ስራ አመራር ቦርዱ በሚያሳልፋቸዉ ዉሳኔዎች ሁሉ አባላት የግል ፍላጎትን ወይም ከቦርድ አባላት ጋር ቅርርብ ያላቸዉ ግልሰቦች ፍላጎትን ማንፀባረቅ የለባቸዉም
- አንድ የቦርድ አባል ከእርሱ ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ዉሳኔ በሚፈልጉ አጀንዳዎች ወይም የጥቅም ግጭት እንዳጋጠመዉ ወይም እንደሚያጋጥመዉ ከገመተ ራሱን ከዉሳኔ ማግለል አለበት
- የቦርድ አባላት በማናኛዉም ሁኔታ ጉቦ፤ ኮሚሽን ወይም ህጋዊ ያልሆነ ጥቅም መቀበል የለባቸዉም
- ሁሉም አባላት በስራ ምክንያት የሚያዉቋቸዉን ምስጢሮች  መጠበቅ ይኖርባቸዋል፤
- የስራ አመርር ቦርድ አባላት ከሆስፒታሉ ስራ አስኪያጅ ጋር በሚኖራቸዉ ግንኙነት በሆስፒታሉ ስራ አስኪያጅ ላይ ማናኛዉንም አሉታዊ ተፅእኖ መፈፀም ወይም እንዲፈፅም ማድረግ የለባቸዉም፡፡

## 12. የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ እና የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ የሥራ ግንኙነት

- በሁለቱ አካላት መካከል ሊኖር የሚገባዉ የስራ ግንኙነት ባላቸዉ የአመራርነት ሚና የሚማማሩበት እና የሚደጋገፉበትን እድል ይፈጥራል፤ ሆስፒታሉም ተገልጋዩ እና ሰራተኛዉ ለሚያነሳቸዉ ጉዳዮች እና መፍትሄዎቻቸዉ ላይ በጋራ ለመስራት እና ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል፡፡

- የሆስፒታሉ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ከሆስፒታሉ ስራ አስኪያጅ ጋር በጋራ በመሆን አጀንዳ  ይቀርፃል፣ የስብሰባ ጥሪ አስቀድሞ ያሳውቃሉ፡፡

- በሆስፒታሉ የሚጠበቁ አገልግሎቶች እና በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ላይ ወቅታዊ መረጃ መለዋወጥ፤ወቅታዊ ዉሳኔ እንዲሰጥ ከተለያዩ አካላት ጋር በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በአጠቃላይ የሆስፒታሉን ራዕይ እና ተልዕኮ   ለማሳካት ምቹ የሆነ የስራ ቦታ መፍጠር የሰራተኛዉን እና የሆስፒታሉን ግንኙነት በማጠናከር ህብረተሰቡ የሚፈልገዉ የአገልግሎት ጥራት እንዲረጋገጥ ተልቅ ሃላፊነት አለባቸዉ፡፡

## 13. የስራ አፈጻጸም ምዘና

በየደረጃዉ ያለዉ አካል የተቋሙን ግብ ለማሳካት ከተቀመጠዉ እቅድ አንፃር ተጠያቂነትን ሊያሰፍን የሚችል የአፈፃፀም ምዘና ስረዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ የሆስፒታሉ ስራ አመራር ቦርድም ከሆስፒታሉ በረጅም እና አጭር ጊዜ ሊደርስበት ካቀደዉ ግብ በመነሳት በቀጣይነት ቢያንስ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ቦርዱ ራሱን እና የሆስፒታሉን ስራ አስኪያጅ አየመዘነ እና የማሻሻያ መርሃ ግበር እያስቀመጠ መሄድ አለበት፡፡

### 13.1. የቦረድ አባላት ምዘና (በጥቅል እና በተናጠል)

ስራ አመራር ቦርዱ በየግዜዉ ስራዉን በሚገባ እያከናወነ ስለመሆኑ ራሱን እንደ አካል (አባሪ 2)እና አባላትን በተናጠል *(ኣባሪ 3)* በተመለከተዉ መሰረት በየስድስት ወሩ ከተመዘገበዉ የእቅድ አፈፃፀም ዉጤት አንጻር መገምገም ይኖርበታል፡፡ ዝቅትኛ ዉጤት የስመዘገቡ አባላት ካሉ ድጋፍ ያደርጋል፤ ይሁን እእጂ በተከታታይ 2 ጊዜ ዝቅተኛ ዉጤት ያስመዘገቡ አባላትም ሆነ የሆስፒታል ቦርድ ካለ በአዲስ እንዲቋቋም/አባላት እንዲተኩ ያስወስናል፡፡ አጠቃላይ የስራ አመራር ቦርዱ የአፈፃፀም ዉጤትም በማህበረሰብ እና በሰራተኛ የዉይይት መድረክ ላይ እንዲተች ማድረግ አለበት፡፡

### 13.2. የሆስፒታል ስራ እስኪያጅ ምዘና

የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ/ስራ አስፈፃሚ ቦርዱ በሚያስቀምጠዉ አቅጣጫ መሰረት ሆስፒታሉን በበላይ በመምራት እና በማስተባበር ከተቀመጠለት እቅድ አንፃር *በኣባሪ 4* እና 5 በተመለከተዉ መሰረት የሚሰጠዉን አቅጣጫ እና ዉሳኔ በማስፈፀም እንዲሁም ከቦርድ ሰብሳቢዉ ጋር በተዋዋለዉ የግል እቅድ እና በሆስፒታሉ ስራ አስፈፃሚነቱ ከተመዘገበዉ ዉጤት ጋር በማቀናጀት አፈፃፀሙ በ 6 ወር አንድ ጊዜ መገምገም ይኖርበታል:: የስራ አስኪያጁን የስራ አፈፃፀም ለመመዘን እና በተገኙ ክፍተቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን በማስቀመጥ የቅርብ ድጋፍ ለማድረግ የቦርዱ ሰብሳቢ ቀዳሚ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተከታታይ 2 ጊዜ ዝቅተኛ ዉጤት ካስመዘገበ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ቦርዱ ለሰየመዉ አካል ሪፖርት ይልካል፤ ያስወስናል፡፡ ዉጤቱም በሰራተኛዉ እና በማህበረሰብ ወይይት እንዲቀርብ እና እንዲተች መደረግ አለበት፡፡

### 13.3. የስራ አመራር ቦረድ ሰያሚ አካላት ምዘና

በአባሪ 7 በተቀመጠዉ መሰረት በየደረጃዉ ያሉ ሰያሚ አካላት የሉበትን የአፈፃፀም ደረጃ በራሳቸዉ ወይም ዉጫዊ አካላት ከትትል እና ምዘና የሚያደርጉበት ነዉ፡፡ የምዘና ስርዓቱም ቢያንስ በ 6 ወር አንድ ጊዜ ከጤና ሚኒስቴር ጀምሮ ሰያሚ አካላት በጋራ በሚያደረጉት ጥቅል የአፈፃፀም ግምገማ ወቅት ዉጤቱ እንዲታይ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 14. የሰያሚ አካላት የስራ አመራር ቦርድ የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት

### 14.1. ጤና ሚኒስቴር

የጤና ሚኒስቴር በቀጥታ የሚሰይማቸዉን የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርዶችን እና በጤና ቢሮዎች ስር በሚገኙ ሆስፒታሉች የስራ አመራር ቦርድ ከእቅድ ዝግጅት ጀምሮ በመደገፍ እና በመከታተል ያለበትን የስራ አፈፃፀም ደረጃ የሚሰጥበት እና በቀጣይነት ለዉጥ ያስመዘገቡ ሆስፒታሎች እና የጤና ቢሮዎችን እዉቅና እንዲያገኙ የሚደረግበትን አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

- ጤና ሚኒስቴር በቀጥታ ከሚሰይማቸዉ የሆስፒታል ቦርዶች ጋር በጋራ ያቅዳል/የዉል ስምምነት ይፈራረማል፤ የቦርድ የስራ አፈፃፀም ግምገማ ያካሂዳል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸዉ/ተጠሪ ለሆነዉ አካል ሪፖርት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

- የክልል የጤና ቢሮዎች የሚሰይሙት የሆስፒታል ቦርድ ያለበትን የአፈፃፀም ደረጃ ጤና ሚኒስቴር በሚመራዉ በቢሮ ሃላፊዎች ወርሃዊ ስብሰባ እና በሚያወጣዉ ፕሮግራም መሰረት ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- የክልሎች አዋጅ እና መመሪያ እንደ ሁኔታዉ የሚለያይ ቢሆንም በተዘጋጀዉ የአገልግሎት ማሻሻያ ማኑዋል መሰረት በክልሎች በሚገኙ ሆስፒታሎች ቦርድ መደራጀቱን ፤ የጋራ እቅድ መዘጋጀቱን/የዉል ስምምነት ሰነድ በጋራ መፈራረማቸዉን እና የአፈፃፀም ግምገማ መደረጉን ክትትል ያድረጋል፡፡
- አጠቃላይ የሆስፒታሎች ቦርድ በተቀመጠላቸዉ የአፈፃፀም መመሪያ መሰረት የሉበትን ደረጃ ከክልል ጤና ቢሮ ሃላፊዎች ጋር ቢያንስ በአመት 2 ጊዜ የአፈፃፀም ግምገማ ያደርጋል፤ ከሰየማቸዉ ቦርዶች ጋር ተመሳሳይ ትባራትን ያከናዉናል፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰይመዉ ቦርድ አፈፃፀም ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ካሉ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመሆን የድጋፍ መርሃ ግብር በማዉጣት ድጋፍ ያደርጋል፤ የሚቀመጡ የማስተካከያ አማራጮች እንደተጠበቁ ሆኖ በተከታታይ 2 ጊዜ ዝቅተኛ ዉጤት ያስመዘገበ ስራ አመራር ቦርድ/አባል ካለ የተሰጠዉን ሃላፊነት እንዳልተወጣ ተቆጥሮ ቦርዱ በአዲስ እንዲቋቋም/አባላት እንዲተኩ ያደርጋል፤ በሌሎች ሰያሚ አካላትም እየተከናወኑ ያሉ የድጋፍ እና የዉሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን ክትትል ደርጋል ፡፡
- የተሻለ አፈጻፀም ያስመዘገቡ የክልል የጤና ቢሮዎች እና የሰየማቸዉን የሆስፒታል ቦርዶች እዉቅና ይሰጣል፡፡

## 14.2. የክልል ጤና ቢሮዎች/ከተማ አስተዳደር /የዞን/ክፍለ ከተማ ሰያሚ አካላት

- በክልሉ አዋጅ እና በተዘጋጀዉ መመሪያ መሰረት የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርዶችን ሊሰይም ይችላል፤ከሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ ጋር የዉል ስምምነት/የጋራ እቅድ ይፈራረማል፡፡
- አጠቃላይ የሆስፒታሎች ስራ አመራር ቦርድ በተቀመጠላቸዉ የአፈፃፀም መለኪያ መሰረት ያሉበትን ደረጃ ቢያንስ በአመት 2 ጊዜ የአፈፃፀም ግምገማ ያደርጋል፡፡
- በቦርዱ አፈፃፀም የሚታዩ ክፍተቶች ካሉ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመሆን የድጋፍ መርሃ ግብር በመዉጣት አስፈላጊዉነን ድጋፍ ያደርጋል፤ የሚቀመጡ የማስተካከያ አማራጮች እንደተጠበቁ ሆኖ በተከታታይ 2 ጊዜ ዝቅተኛ ዉጤት ያስመዘገበ ስራ አመራር ቦርድ/አባል ካለ የተሰጠዉን ሃላፊነት እንዳልተወጣ ተቆጥሮ ቦርዱ በአዲስ እንዲቋቋም/አባላት እንዲቀየሩ ያደርጋል፡፡
- የተሻለ አፈጻፀም ያስመዘገቡ የሆስፒታል ቦርድ እና አባላትን እዉቅና ይሰጣል፡፡

## 15. ማጣቀሻዎች /References


- የሆስፒታል አፈፃፀም ክትትል እና ማሻሻያ ማኑዋል (HPMI) 2010 ዓ/ም ( 2017/18 G.C)
- የኢትየጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ጤ.ዘ.ት.ዕ) 2008 – 2012 ዓ/ም
- የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች አገልግሎት ትራንስፎርሜሽን ማኑዋል 2007 ዓ/ም
- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር  የጤና ክብካቤ የሃብት ማግኛ ሪፎርም ማስፈፀሚያ ማኑዋል 2005 ዓ/ም
- የፌደራል እና ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች አገልግሎት ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 167/2001ዓ/ም

- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የጤና ክብካቤ ገንዘብ ማግኛ ስልት 19 91 ዓ/ም

## 16. አባሪ፡

ይህን ማኑዋል በማስፈፀም በየደረጃዉ ያሉ የሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድ ሰያሚ አካላት፤ የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድ እና የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ በአፈፃፀም ያሉበትን ደረጃ ለመመዘን ዉስጣዊም ሆነ ዉጫዊ አካላት ሊጠቀሙ የሚችሉበት የመመዘኛ ቸክሊስቶች በአባሪነት እንዲያያዙ ተደረጓል፡፡ በሁሉም ዘርፍ የምዘና ሂደቱ በሚከናወንበት ወቅት የተገኙ ክፍተቶችን ለማሻሻል የሚቀጥለዉን መደበኛ ስብሰባ እና የአፈፃፀም ግምገማ ጊዜ ታሳቢ ያደረገ የድርጊት መርሃ ግብር መቀመጥ ይኖርበታል፤ በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ መከናወን የነበረባቸዉ ተግባራትም ያሉበተ ደረጃ በመደበኛ ስብሰባ ወቅት የሚታይ ይሆናል፡፡

## አባሪ 1፡ የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ ስራ አፈፃፀም መከታተያ ቸክ ሊስት

ይህ የመከታተያ ቸክሊስት በስራ አመራር ቦርዱ የሆስፒታሉን ስራ አስኪያጅ ጨምሮ የጋራ እና የተናጠል የስራ ድርሻ እና ሃላፊነቶችን በማስፈፀም የተቀመጡ ነጥቦች ላይ መነሻ ያደረገ ነዉ::

| ተ.ቁ | የመለኪያ ነጥቦች | ማረጋገጫ ነጥቦች | የማረጋገጫ መንገድ | አለ | የለም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሥራ አመራር ቦርድ አደረጃጀት እና ምደባ | • የቦርድ አባላት የምደባ ደብዳቤ ከሚመለከተዉ ባለስልጣን /ሰያሚ አካል የተሰጠ አለ? | • የምደባ ደብዳቤ ማየት | | | |
| | | • የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አመራረጥ በፌድራል ወይም በክልል የወጣውን አዋጅ/መመሪያ የማስፈፀሚያ ማኑዋል መሠረት ባደረገ መልኩ ነዉ? | የመረጣ ሂደቱ ከተቀመጠዉ አዋጅ/መመሪያ/ማኑዋሊጋር የተጣጣመ መሆኑን ማየት | | | |
| | | • የተመረጡ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ዝቀተኛዉን የመመዘኛ መስፍረት አሟለተዋል? | መስፈረቱን ማሟላታቸዉን ዉይት ተደርጎ በሰራተኛዉ/በማህበረሰቡ መረጣ የተካሄደ መሆኑን ማረጋገት | | | |
| | | • በቦርዱ የተዘጋጀ የዉስጥ አሰራር መግባቢያ ሰነድ አለ | የተዘጋጀ የአሰራር መግባቢያ ሰነድ ማየት እና ተግባራዊነቱን ከይዘቱ ጋር ማመሳከር | | | |
| | | • በቦርዱ የተዘጋጀ የረጅም ጊዜ እቅድ አለ<br>• በሥራ አመራር ቦርድ አባላት የተዘጋጀ አመታዊ የሥራ እቅድ አለ? | የተዘጋጀዉን የረጅም ጊዜ እና አመታዊ እቅድ ማየት<br>እቅዱ በተቀመጠዉ መሰረት መፈፀሙን ከዉስጥ ይዘቱ ጋር የተሰሩ ስራዎችን ማመሳከር | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | የሥራ አመራር ቦርዱ የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ | • የሥራ አመራር ቦርዱ የሆስፒታል ራዕይ፣ ተልኮና እሴቶችን ሰራተኞች ግንዛቤዉ እንዲኖራቸዉ አድርጓል? | ግንዘቤ የተሰጠበት መረጃ ማየት፤ የቦርድ አባላትን በጥያቄ ማረጋገጥ | | | |
| | | • ቦርዱ የጊዜ ሰሌዳዉን በጠበቀ መልኩ ስብሰባ አድርጓል | በበጀት ዐመቱ የተዘጋጀ መግባቢያ ሰነድ እና ተግባራዊነቱን፤ ቃለ-ጉባኤ ማየትና ማረጋገጥ | | | |
| | | • አባላት በምልዓተ - ጉባኤዉ መሰረት በስብሰባዉ ላይ ይገኛሉ | ቃለ-ጉባኤዉን በማየት ማረጋገጥ | | | |
| | | • የመወያያ አጀንዳዎች ቀድመዉ ተዘጋጅተዉ ለቦርድ አባላት እንዲደርሱ ተደርጓል? | ሂደቱን መመልከት፤አባላትን መጠየቅ | | | |
| | | • የሥራ አመራር ቦርዱ አመታዊ የሥራና የበጀት አቅዱን የማጽደቅ ተግባር በወቅቱ አከናዉኗል? | ቦርድ፤ ሰራተኛዉ እና ማህበረሰቡ የተሳተፉበት የጸደቀዉን የሥራና በጀት እቅድ ማየት | | | |
| | | • የሥራ አመራር ቦርዱ የሩብ ዓመት የሥራና የበጀት እቅድ አፈጻጸም በወቅቱ ይገመግማል? | የገመገመበትን ሪፖረትና የሰጣቸዉን አስተያየቶች እንዲሁም ተግባራዊነቱን ማየት | | | |
| | | • የሥራ አመራር ቦርዱ የስብሰባ የጊዜ ሠሌዳዉን በግልጽ በሆስፒታሉ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ሌሎች እንዲያዉቁት ያደርጋል? | ቀሪ የሥብሰባ ፕሮግራሙንና ቃለ ጉባኤዉን አይቶ ማረጋገጥ<br>የጊዜ ሰሌዳዉ ላይ በሁሉም አባላት መስማማት ላ መደረሱን ማረጋገጥ<br>በተጻፈዉ መሰረት ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የሥራ አመራር ቦርዱ እና በተለያየ ምክንያት በሚጓደሉ አባላት ምትክ ለሚመደቡ አባላት ሥልጠና የመስጠት እቅድ አለዉ? | የተዘጋጀዉን የሥልጠና እቅድ ማየት<br>በእቅዱ መሰረት ተግባራዊነቱን (ስልጠናዉ በተገቢዉ መከናወኑን) ማረጋገጥ ........... | | | |
| 3 | የሥራ አመራር ቦርዱ ተጠያቂነት ከማስፈን አንጻር | ከሚመለከታቸዉ አጋር አካላት እና ማህበረሰብ ጋር በመሆን ተገቢ ዉይይት በማድረግ የሚነሱ ጉዳዮችን ለመፍታትና ለማሻሻል የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጃል? | የተዘጋጀዉን የድርጊት መርሃግብረ በማየት ማረጋገጥ<br>የድርጊት መርሃ ግብሩ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ | | | |
| | | የሥራ አመራር ቦርዱ ከተገልጋዩና ከሰራተኛዉ የሚነሱ ቅሬታዎችን በመፍታት የተሰጠ ግብረ መልስ አለ? | ቀሪ የተሰጡ ግብረመልሶችን በማየት ማረጋገጥ<br>የተነሱ ጉዳይዎች መፈታታቸዉን ማረጋገጥ | | | |
| | | የሥራ አመራር ቦርዱ የአከናወናቸዉን ተግባራት በወቅቱ ለሚመለከተዉ አካል የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሪፖርት ያቀርባል | ቀሪ ወቅታዊ ሪፖርት መመልከት<br>ሪፖርቶች ቅድሚያ በየደረጃዉ ባሉ አካላት ተገምግመዉ የቀረቡለት መሆኑን እና ቦርዱ በጥልቀት ገምግሞ የላከ መሆኑን ማረጋገጥ | | | |
| | | የሥራ አመራር ቦርዱ የስነ-ምግባር መተዳደሪያ ደንብ አለዉ? | የተዘጋጀዉን የሥነ-ምግባር እና መተዳደሪ ደንቡን ማየት<br>አባላት በደንቡ ላይ መስማማተቸዉን ማረጋገጥ<br>ያጋጠሙ የስነምግባር ጉድልቶች ካሉ የተወሰደዉን ማሰተካከያ ካለ ማረጋገጥ | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሥራ አመራር ቦርዱ የዉስጥና የዉጭ የሂሳብ ኦዲት ሪፖረት ይደርሰዋል? | የተደረገለትን ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ማየት<br>የዉጭ ኦዲት በውቅቱ እንዲደረግ ያደረገዉ ጥረት ካለ ማየት<br>በዉጭም ሆነ በዉስጥ በተገኙ የኦዲት ክፍተቶች ላይ የተወሰደ ማስተካከያ መደረጉን ማረጋገጥ | | | |
| 4 | የሥራ አመራር ቦርዱ የሆስፒታሉን ከፍተኛ አመራር እና የሆስፒታሉን ስራ አስኪያጅ ሌሎችን ኮሚቴዎችን ማደራጀት | የሥራ አመራር ቦርዱ የሆስፒታሉን ስራ አስኪያጅ የሚመለከተዉን የስራ ዝርዝርን በእቅድ ላይ እንዲፈራረም ያደርጋል; | የተፈራረሙበት ዉል/ሰነድ ማየት<br>በዉሉ መሰረት የእቅዱ ተግባራዉነትን ማረጋገጥ | | | |
| | | የሥራ አመራር ቦርዱ የሆስፒታሉን ስራ አስኪያጅ አፈጻጸምን በየ 6 ወር ባፈራረመዉ መሰረት ይገመግማል ወይ | የግምገማ ዉጤት፤ቃለ ጉባኤ፤ ሪፖርትማየት<br>የምዘና ስርዓቱ የሁሉም አካል ዉሳኔ ያረፈበት እና የማስተካከያ አስተያየቶች ተግባራዊነት ማረጋገጥ | | | |
| | | ቦርዱ ማኔጅመንት ኮሚቴ አባላትን የአባልነት የክፍሎችን ዉክልና ተዋፅዖ አፅድቋል;; | አስፈላጊ የስራ ክፍሎች መካተታቸዉን ማረጋገጥ፤<br>የሆስፒታል የማኔጅመንት አባላት የሚወከሉበትን የስራ ክፍል ያፀደቀበት ማስረጃ ላይ ምልከታ ማድረግ(ደብዳቤ፤ቃለ ጉባዔ፤.....) | | | |
| | | የሥራ አመራር ቦርዱ የሆስፒታሉን ማኔጅመንት ኮሚቴ አፈጻጸሙን ይከታተላል(የምዘና ሂደቱን ትክክልኛነት ያረጋግጣል);; | የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ማረጋገጥ (በእቅድ በተቀመጠዉ መሰረት ወጥነቱን ማየት) | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በበላ አካላት በግብረ መልስ የተነሱ ማስተካከያዎች ተግባራዊነት ማረጋገጥ | | | |
| 5 | አጠቃላይ የሆስፒታሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ትግበራ እና ቀጣይነት ያለዉ ግምገማና ክትትልን በተመለከተ | የሥራ አመራር ቦርዱ በአገር አቀፍ ደረጃ በተቀመጡ የአገልግሎት ማሻሻያ መለኪያዎችን መተግበራቸዉን በቅርበት እና ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ወቅቱን ጠብቆ ይገመግማል፤ ይደግፋል፤ዉሳኔ ይሰታል;; | በቦርድ ስብሰባ **ቋሚ አጀንዳ** መሆናቸዉን ከስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ማረጋገጥ፡<br>➢ **የሃብት ማግኛ ሪፎርም እቅድ ትግበራ እና የሆስፒታል አገልግሎት ትራነስፎርሜሽን መመሪያ ትግበራ (EHSTG met %)**<br>➢ **የቁልፍ አፈፃፀም መለኪያዎች እና አመላካቾች (KPIs and HMIS)**<br>➢ **የትራት ትራንስፎርሜሽን አፈፃፀም (HSTQ)**<br>➢ **የቀዶ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም ደረጃ (SaLTS)**<br>➢ **ፅዱ፤ ምቹ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ሆስፒታል መፍጠር (CASH)**<br>➢ **ከህምም ነፃ ሆነ የሆስፒታል መፍጠር (Pain Free Hospital Initiative)**<br>➢ **የገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ( HCF)** | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ➢ የሆስፒታል የክላስተር እንቅስቃሴ<br>( EHAQ)<br>➢ የጤና ተቋሙን የሥራ ላይ ጉብኝት ውጤት ማየት<br>➢ የመልካም አስተዳደር ጉዳይዎች የለበት ደረጃ (GGI)<br>➢ ሌሎች አጀንዳዎች ……. | | | |

## አባሪ - 2 ፡ የሆስፒታል ቦርድ የጥቅል መመዘኛ ነጥቦች

ከታች የተቀመጡ የመመዘኛ መስፈርቶች እንደ ሁኔታዉ በክልሎች እና በፌደራል ደረጃ በየዐመቱ በሚቀመጡ ግቦች ሊለያዩ ይችላሉ፤ የስራ አመራር ቦርዱ የስራ አፈጻፀም ምዘና በ 6 ወር አንድ ጊዜ የሚካሄድ ከሆነ እና በየሩብ ዓመቱ የተሰበሰቡን መረጃዎች የሚጠይቁ መለኪያዎች ካሉ የሁለቱ ሩብ ዐመት አማካይ ዉጤት ተወስዶ የሚሰላ ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የመመዘኛ ነጥብ | 1 | 2 | 3 | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጥቅል የሆስፒታሉ አፈፃፀም ከእቅድ አንፃር ሲታይ | ከ 80 % በታች | ከእቅድ ከ 80 - 90 % | የእቅድ ከ 90 – 100 % | |
| 2 | በሆስፒታሉ ካሉት(ሆ/ሉ ትርጉም ሰጥቶ ካስቀመጣቸዉ) የህ/መሳሪዎች መካከል በ 6 ወሩ አገልግሎት የማይሰጡ የህ/መሳሪያዎች በ %(KPI) | >5 % | <5% | 0% | |
| 3 | የሆስፒታሉ ፅዱነት፤ምቹነት እና ደህንነቱን የማረጋገጥ መለኪያ በ %(KPI) | ቀይ | ቢጫ | አረንጓዴ | በስሌቱ መሰረት በ% ይቀመጣል |
| 4 | ከተወለዱ በ 24 ሰዓት ዉስት የጨቅላ ህፃናት ሞት ምጣኔ በ % (HMIS ) | >1% | < 1% | 0% | |
| 5 | በወሊድ ምክንያት የሞቱ እናቶች ምጣኔ በ % (HMIS) | >1% | < 1% | 0% | |
| 6 | የሆስፒታሎች አገልግሎት ትራንስፎርሜሽን መመሪያ ትግበራ በ % | <85% | 85-94.9% | >95% | |
| 7 | በባለፈዉ 6 ወር የተካሄዱ የሆስፒታል ምልከታ በቁጥር *(በማስረጃ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ እና ግብረ መልስ)* | ተካሂዷል(ያልተካሄደ ከሆነ 0 ነጥብ ያገኛል) | ተካሂዷል፤የታዩ ክፍተቶች | ተካሂዷል፤ የታዩ ክፍተቶች ሙሉ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | በከፊል ተፈተዋል | በሙሉ ተፈተዋል | |
| 8 | በባለፈዉ 6 ወር የተካሄዱ የማህበረሰብ ዉይይት በቁጥር *(በማስረጃ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ)* | ተካሂዷል(ያልተካሄደ ከሆነ 0 ነጥብ ያገኛል) | ተካሂዷል፤ የተነሱ ጥያቄዎች በከፊል ተፈተዋል | ተካሂዷል፤ የተነሱ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ተፈተዋል | |
| 9 | የሰራተኛ እርካታ በ % *(በማስረጃ የተደገፈ የድርጊት መርሃ ግብር እና የተወሰዱ ማሻሻያዎች)* | ተካሂዷል(ያልተካሄደ ከሆነ 0 ነጥብ ያገኛል) | ተካሂዷል፤ የተነሱ ጥያቄዎች በከፊል ተፈተዋል | ተካሂዷል፤ የተነሱ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ተፈተዋል | |
| 10 | የተገልጋይ እርካታ በ % *(በማስረጃ የታዩ የድርጊት መርሃ ግብር እና የተወሰዱ ማሻሻያዎች)* | ጥናት ተካሂዷል፤የመሻሻያ እቅድ የለም | ጥናት ተካሂዷል፤ የመሻሻያ እቅድ አለ፤በከፊል ተተግብሯል | ጥናት ተካሂዷል፤ የመሻሻያ እቅድ አለ፤በከፊል ተተግብሯል | |
| | ጠቅላላ ዉጤት*(ከ 30 የተገኘዉ ዉጤት ከ 100% ተቀይሮ ይቀመጣል)* ፡<br><br>ከ 10 በታች ዝቅተኛ ፤ ከ 10 እስከ 15 አጥጋቢ፤ 16 እስከ 20 - መካከለኛ፤ ከ 21 እስከ 25 ከፍተኛ፤ ከ 26 – 30 - በጣም ከፍተኛ | 10 | 20 | 30 | |

## አባሪ- 3 የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ አባለት የግል የመመዘኛ ቅጽ

| ተቁ | የመመዘኛ ነትቦች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቦርድ አባል የሆስፒታል ራዕይ፤ተልዕኮ በሚገባ ይገነዘባል፤ለሌሎች ያስረዳል ሌሎች የማሻሻያ ፕሮግራሞችን/ሪፎርሞችን አንብቦ በመምጣት አዳዲስ ሃሳቦችን ያቀርባል | | | | | | |
| 2 | እንደ ሥራ አመራር ቦርድ በአባልነት የሚጠበቅበትን የሥራ ድርሻ ተገንዝቧል፤ተግባራዊ ያደርጋል፤የተሰጡ ጠቤት ስራዎችን በወቅቱ ፈፅሞ ያቀርባል | | | | | | |
| 3 | የሥራ አመራር ቦርዱ የስብሰባ ጊዜ ከመደረሱ በፊት አጀንዳዎችን አንብቦ እና በቂ ዝግጅት አደርጎ ይቀርባል፤አዳዲስ ሃሳቦችን ያፈልቃል | | | | | | |
| 4 | ከሌሎች ከሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ጋር መልካም ግንኙነት አለዉ፤ ከሳኣት አጠቃቀም ጀምሮ የመተዳደሪያ ደንቦችን እና የስነምግባር ደንቦችን በሚገባ ይፈፅማል | | | | | | |
| 5 | ስለ ሆስፒታሉ አገልገሎቶችም ሆነ ፕሮግራሞች በቂ ግንዛቤ ለሰራተኛዉ እና ለተገልጋዩ ማ/ብ ያስጨብጣል( በማስረጃ የቀረበ) | | | | | | |
| 6 | የሆስፒታል የፋይናንስ አሰራር፤ ሌሎች መመሪያዎችን በአግባቡ ተገንዝቧል፤የአሰራር ግድፈት እንዳይፈጠር ሃሳብ ያቀርባል፤ይደግፋል | | | | | | |
| 7 | የሥራ አመራር ቦርዱ ለስብሰባ በተያዘዉ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ባለማቆራረጥ ተሳትፎ ያደርጋል | | | | | | |
| 8 | እንደ ሥራ አመራር ቦርደ በአባልነቱ የሆስፒታሉን መልካም ገጽታ ለመገንባት ለህበረተሰቡ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ግንዛቤ እንዲኖረዉ የማድረግ ተግባር ያከናዉናል ( በተግባር በምሳሌ የሚገለፅ) | | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | ሆስፒታሉ፤ ሰራተኛዉ እና ተገልጋዩ ማ/ብ መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸዉ በግሉ ያከናወነዉ ተግባር | | | | | | |
| 10 | በአባልነቱ በሥራ አመራር ቦርድ ቀርበዉ ዉይይት የተደረገባቸዉን ጉዳዮች ምስጥራዊነት ይጠብቃል | | | | | | |
| 11 | በቦርድ አባላት መካከል አለመግባብት ሲኖር ችግሩን ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፤በተለያ አጋጣሚዎች በሆስፒታሉ በመገኘት በግሉ በሆስፒታሉ አጠቃላይ በሉ ሁኔታዎች ላይ ምልከታ አድርጎ ግብረ መልስ ይሰታል( በማስረጃ የቀረበ) | | | | | | |
| 12 | የሥራ አመራር ቦርዱን ኃለፊነትና ተግባር፤ የራሱን ሃላፊነት እና ተግባር በሚገባ ጠንቅቆ ያዉቃል ፤ እንዲሁም የተሰጠዉን ስራ በተገቢዉ በወቅቱ ይፈጽማል | | | | | | |
| | ***ጠቅላላ ዉጤቱ 5 ደረጃዎች ያሉት ሲሆን ፡***<br><br>*ከ 60 የተገኘዉ ዉጤት ወደ 100 % ተቀይሮ ይቀመጥለታል፡*<br><br>*ዝቅተኛ (ከ 12 በታች)፤አጥጋቢ(ከ 12 -23)፤መካከለኛ(ከ 24 -35)፤ ከፍተኛ(ከ 36 እስከ 47) በጣም ከፍተኛ ( ከ 48 -60) ተደርጎ እንዲያዝለት ይደረጋል* | **12** | **24** | **36** | **48** | **60** | |

## አባሪ-4 የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ መመዘኛ ቅጽ (ክፍል-1 ከ 75 %)

የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ምዘና እንደየክልሉ አዋጅ እና መመሪያ የሚለያይ እና የምዘና ስርዓቱ ሌላ ይዘት የሚኖረዉ ከሆነ በዚህ ማስፈፀሚያ ማኑዋል የተካተቱ ነጥቦች በእቅዱ መካተታቸዉን ቦርዱ ማረጋገጥ አለበት፤ የነጥብ አሰጣጡም በተመሳሳይ ከክልሉ ወይም ከሆስፒታሉ የሰራተኛ የስራ አፈፃፀም ስርዓት ጋር መጣጣም ይኖርበታል፡፡ የዉጤት አሰጣጥ ስሌት ሂደቱም ከላይ በስራ አመራር ቦርዱ የምዘና ነጥቦች ስር የተቀመጡ ሃሳቦች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ስራ አስኪያጁም ከዚህ በታች በተቀመጡት መለኪያዎች ከ 10 – 55 የሚጠበቁት ነጥቦች እናዳሉ ሆኖ ከ 55 የተገኘዉ ነጥብ ከ 100% ከተሰላለት በኋላ ከ 100% ያገኘዉ ዉጤት እንደገና ለክፍል 1 መመዘኛ ከ 75% ተሰልቶ እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ ስሌት ከታች በክፍል 2 ለተቀመጡ መመዘኛዎች ከተቀመጡለት ነጥቦች ከ 25 ያገኘዉን ዉጤት ከ100% ከተቀየረለት በኋላ የተገኘዉ ነጥብ እንደገና ወደ 25% ተቀይሮ በሁለቱ ቅፆች(ክፍል 1 እና ክፍል 2) ያገኘዉ ነጥብ ድምር እንዲቀመጥለት ይደረጋል ፡፡ በክፍል 1 መመዘኛ ለተቀመጡ የመለኪያ ነጥቦች ከ 1 -5 ደረጃ ከመሰጠቱ በፊት የማረጋገጫ ነጥቦችን በማስረጃ አስደግፎ እያንዳንዳቸዉን ከ 1 -5 ደረጃ በመስጠት የድምሩ አማካይ ወጤት የመለኪያ ነጥቡ ደረጃ ተደርጎ የወሰዳል፡፡

| ተ.ቁ | የመለኪ ነጥቦች (ስታንዳርዶች) | ማረጋገጫ ነጥቦች ( መስፈርቶች) | ለመለኪያ ነጥቡ የተሰጠ ደረጃ | | | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | |
| 1. | **ከስራ አመራር ቦርድ ጋር ያለዉ ተግባቦትና ግኑኝነት** | • የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ከስራ አመራር ቦርድ ጋር በመሆን የረጅም እና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ያዘጋጃል ?(ይዘቱን እና በተግባር የተሰሩ ስራዎችን ማመሳከር) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ለቦርዱ ወቅታዊ መረጃን ይሰጣል ? | | | | | | |
| | | • የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ለቦርዱ አባላት አስፈላጊዉን ክህሎትና ዕዉቀት እንዲያገኙ ሥልጠናዎች ያመቻቻል ፤ይተገብራል (እቅድ እና ትግበራዉን ማመሳከር) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ በማህበረሰቡ እና በሆስፒታሉ ሰራተኞች መካከል ዉጤታማ /መልካም የሆነ ግኑኝነት እንዲኖር ያደርጋል ? (በተጨባጭ በእቅድ ተይዘዉ የተከናወኑ ተግባራት) | | | | | | |
| 2. | **ዕቅድ፤ሪፖርት፤ ክትትል** | • የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ የተቋሙን የአምስት ዓመት እና የዓመት እቅድ አዘጋጅቶ ለህ/ቡ እና ለሰራተኛዉ ያስተቻል ?(ቃለ ጉባኤ፤ሰነድ ይመልከቱ) | | | | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ የፋይናንስና ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎችን ሪፖርት ለቦርድ እና ለሚመለከተው የበላይ አካል ወቅቱን ጠብቆ ይልካል ?(ሪፖርቶች ከስራ ክፍሎች ጀምሮ በጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ መደበኛ የሆነ የማናጅመንት ስብሰባ ያካሂዳል፤ ችግሮችን በጋራ ይለያል፤ ግብረ መልስ ሳይቆራረጥ ይሰጣል ? | | | | | | |
| 3. | **የሂሳብ እና በጀት አጠቃቀም** | • የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ የበጀት ዕቅድ አዘጋጅቶ ለቦርድ በማቅረብ እንዲጸድቅ ያደርጋል ወይ? | | | | | | |
| | | • የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ከቦርድ ጋር በመሆን የውስጥ ገቢን ለማሳደግ ያቅዳል፤ አቅጣጫ ያስቀምጣል ? (በተገኘዉ ገቢ የተገኘ ተጨባጭ ለዉጥ ) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ የተቋሙን የፋይናንስ አፈጻጸም በተቀመጠው የመንግስት መመርያ መሰረት መከናወኑንና ለሚመለከተው ለቦርድና ለሌሎች የበላይ አካላት በተቀመጠው ጊዜ መሰረት ያቀርባል ወይ?(የአሰራር ክፍተት አለመኖሩን ያረጋግጡ) | | | | | | |
| 4. | **የሆስፒታል ማናጅመንት ኮሚቴ እና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴ** | • የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ውጤታማ የማኔጅምንት አባላትን ከስምምነት ሰነድ ጋር በማዋቀር የተቋሙን የለት እለት ስራ መተገበራቸውን በተቀመጠው የስራ ሰሌዳ መሰረት ይከታተላል ፤ | | | | | | |
| | | • ኮሚቴዎች አቅድ አቅደዉ በእቅዳቸዉ መሰረት ተግባር ላይ ያሉ መሆናቸዉን ይከታተላል(የኮሚቴዎችን እቅድ እና ትግበራዉን ከመግባቢያ ሰነዱ ጋር ማመሳከር ) | | | | | | |
| 5. | **የሰው ሀብትና አመራርና የሙያ እድገት** | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ለተቋሙ የሚያስፈልገው የሰው ሀይል በመመልመልና በተቋሙ እንዲቆዩ ለማድረግ ከቦርዱ ጋር በጋራ ይሰራሉ ወይ (ሰራተኛዉን በሆስፒታሉ ተረጋግቶ በተነሳሽነት በስራ ላይ እንዲዎይ ለማድረግ በተግባር የተሰሩ/እየተሰሩ ያሉ ስራዎች) | | | | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ለተለያዩ ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን የሚያገኙበትን ሥራ ሰርቷል ወይ (የታቀዱ እና በተግባር የተከናወኑ) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ አተቃላይ የሰራተኞች የጋራ መድረክ በቀጣይነት እንዲኖራቸዉ አመቻችቷል ወይ?(ሰራተኛዉ ባነሳቸዉ ጉዳይዎች ላይ በተከናወኑ ተግባራት የተሸሻለ የሰራተኛ የእርካታ ደረጃ ካለ) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ አዳዲስ የሚመጡትን የአገልግሎት ማሻሻይ መመሪያዎችን በቀጣይነት ለሰራተኞች ያስተዋዉቃል ወይ?(በተግባር በእቅድ የተከናወኑ ተግባራት) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ምቹ የሆነ የሥራ አካባቢ የመፍጠር ሥራ ይሰራል ? **(Check staff satisfaction survey result and attrition rate)** | | | | | | |
| 6. | **የአገልግሎት ጥራት የህሙማን ደህንነት** | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የጥራት ማሻሻያ እቅድ፤ኮሚቴ እና ትግበራውን በተቀመጠው ግዜ መሰረት ይገመግማል ? | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ለአገልግሎት ጥራት ማሻሻያ አስፈላጊውን ግብአት ያቀርባል?(የተለዩ ችግሮች፤የተቀረፁ የማሻሻ ፕሮጀክቶች እና የድርጊት መርሃ ግብር አተገባበር) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የሆስፒታሉን ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ከሚከተሉት ቁልፍ አፈጻጸም መለኪዎች እንጻር በቀጣይነት አየገመገመ በተገኙ ክፍተቶች ላይ የመፍትሄ ሃሳብ እያስቀመጠ የሚሄድበት አሰራር አለ ?<br>➢ *EHSTG met %*<br>➢ *All KPIs*<br>➢ HSTQ<br>➢ EHAQ | | | | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ➢ SaLT<br>➢ CASH<br>➢ Pain Free Hospital Initiative<br>➢ የዉስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም<br>➢ የጤና ተቋሙን.የሥራ ላይ ጉብኝት ውጤት<br>➢ GGI(የመልካም አስተዳደር ልኬት/ምዘና ዉጤት)<br>➢ Others (RHB, በሰያሚ አካላት የተያዙ የትኩረት አቅጣጫዎች…) | | | | | | |
| 7. | **መመሪያ እና ደንቦችን ትግበራ** | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ በጤናዉ ሴክተር የሚተገበሩ መመሪያ እና ደንቦችን በሕግና መመሪያዉ መሰረት መተግበራቸዉን ይከታተላል ? (የሥራ ላይ ደህንነት፤የቅጥር ፤የሂሳብ አያያዝ፤ኦዲት …) | | | | | | |
| 8. | **የተቋም አስተዳደር(ምድረ-ግቢ)** | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የተቋሙን ህንጻ፤የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች እና ተሸከርካሪ በአግባቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ተገቢ እንክብካቤ እንዲደረግ ያደርጋል ወይ(በተግባር የተከናወኑ ተግባራት) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ለህሙማንና ለሰራተኞችን ንጹህ፤ምቹ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ ይሰራል ወይ? (የ ‘CASH’ ትግበራ በስታንዳርዱ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ) | | | | | | |
| 9. | **ከባለድርሻ አካላት ጋር ዉጤታማ የሆነ ግኑኝነት** | • በሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የሆስፒታሉን መልካም የሆነ ገጽታ ለመገንባታና ለመፍጠር የተሰሩ ሥራዎች አሉ ወይ (በማስረጃ የተረጋገጥ) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ከሶስተኛ አካላት ጋር ሆስፒታሉን ወክሎ ስለ ሆስፒታሉ የገፅታ ግንባታ ስራ ይሰራል ወይ?(በማስረጃ የተረጋገጠ) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የህብረተሰቡን ፍላጎት ለሟሟላት ከሚመለከታቸዉ የህብረተሰቡ መሪዎች እና አጋር አካላት ጋር ተቀራርቦ ይሰራል ወይ? (የተገኘ ዉጤት በማስረጃ) | | | | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ  ከህብረተሰቡ ጋር ቢያንስ በ 6 ወር አንድ ጊዜ ሳይቆራረጥ ወቅቱን ጠብቆ ከቦርድ ስብሰባ በፊት ስብሰባ ያካሂዳል ወይ? | | | | | | |
| 10. | **የመሪነት፤አመራር ና የዉሳኔ አሰጣጥ** | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ  ወቅታዊና ችግር ፈቺ ዉሳኔዎችን ይሰጣል ወይ? | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የሆፒታሉን ግብና ዓላማ ለማሳካት በስሩ ያሉትን አጠቃላይ ሰራተኞች ክትትልና ግምገማ፤የማበረታታት ሥራዎችን ይሰራል፤ ይደግፋል፤ ያበቃል ወይ? | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ችግር ፈቺ፤በተግባር ለዉጥ የስመዘገበበት የፈጠራ ክህሎት አለዉ ወይ ?(በተግባር የተገኙ ተሞክሮዎች እና ለሌሎች በክላስተር የተላለፉ) | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ዉጤታማ ስራን ለማከናወን የአንድነት እና የጋራ የመስራት መንፈስ ከመፍጠር አንጻር ያከናወናቸዉ ሥራዎች አሉ ወይ?(በማስረጃ የተረጋገጠ) | | | | | | |
| 11. | **የግል ጥንካሬዎችና ስብዕና** | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ ባላዉ የስራ ግንኙነት እና ዉሳኔ አሰጣት ሰራተኛዉ እምነት አሳድሮበታል፤ ስራ አስኪያጅ ተአማኒነት እና ግልፀኝነትን የተላበሰ ነዉ | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ በአለባበስ ፕሮቶኮል ይጠብቃል፤ ለሌሎች በአርዓነት ሊጠቀስ ይችላል? | | | | | | |
| | | • የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ  ራሱን ለማብቃት ጥረት ያደርጋል፤ ክህሎት፤ልምድ እና ዕዉቀት አለዉ ፤ሌሎችንም ለማስተማር ይጠቀምበታል? | | | | | | |

አባሪ 5፡ የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ መመዘኛ ቅጽ (ክፍል-2 ከ 25 %)

| S.NO | Selected Indicators(መለኪያ/አመላካች) | Value out of 25%( ከ 25 የሚወሰዱት ክብደት) | Grade margin | | | | | | Remarks |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | **0** | **1** | **2** | **3** | **4** | **5** | |
| 1 | % of EHSTG standards met | 5 | Zero standard meet | 1-20% | 21-40% | 41-60% | 61-80% | 81-100% | |
| 2 | Outpatient waiting time to treatment | 2 | Above 60 minutes | 35-60 minutes | Below 35minutes | | | | |
| 3 | ER triaged within 5 minutes | 2 | If > 50% ER pt triaged within 5minutes | If 50-90% ER pt triaged within 5minutes | If above 90% ER pt triaged within 5minutes | | | | |
| 4 | ER length of stay greater than 24 hours | 2 | >10% of pt stay for >24hrs | 0-10% of patient stay for >24hrs | If there is no length of stay for >24hrs | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | Inpatient mortality | 2 | Worsen | Maintain the baseline | Any improvement | | | | |
| 6 | Maternal mortality rate | 3 | Worsen | Maintain the baseline or 1-10% improvement | 10%-50% improved | >50% improved | | | |
| 7 | Neonatal death within 24 hours of delivery | 2 | Worsen | Maintain the baseline or 1-10% improvement | >10% improved | | | | |
| 8 | Staff satisfaction | 2 | If survey is not done | Staff satisfaction 1-5 | Staff satisfaction 6-10 | | | | |
| 9 | Patient satisfaction | 5 | If survey is not done in one of the quarters | patient satisfaction 1-4 & all the quarters done | patient satisfaction 5-6 & all the quarters done | patient satisfaction 6-7& all the quarters done | patient satisfaction 7-8 & all the quarters done | patient satisfaction above 8 & all the quarters done | |

**ማሳሰብያ፡** *የሥራ አስኪያጅ የሥራ አፈጻጸም የግምገማ ዉጤት አሰጣጥ:*

1. *የስራ አስኪያጅ የስራ አፈጻጸም መመዘኛ ቅጸ(አባሪ 4) ከ 75 %*
2. *የስራ አስኪያጅ የስራ አፈጻጸም መመዘኛ ቅጸ(አባሪ 5) ከ 25 %*
3. *አጠቃላይ በሁለቱ ክፍሎች የተገኘዉ የስራ አስኪያጅ የስራ አፈጻጸም ዉጤት ተደምሮ ከ 100 % ይቀመጣል*

## አባሪ 6፡ የሆስፒታል ቦርድ የሆስፒታል መልካም አስተዳደር ኢኒዴክስ መለኪያ ቅፅ (Good Governence Index)

| ተ.ቁ | አመላካቾች | የተሰጠ ክብደት |
|---|---|---|
| | **የህዝብ እሮሮ አመላካቾች** | 50 |
| 1 | **የተገልጋይ እርካታ ደረጃ** | 15 |
| 2 | **ስለ ህመማቸዉ እና** ስለ ህክምና አገልግሎት በቂ መረጃ ያላቸው ህሙማን መጠን | 5 |
| 3 | የታዘዘላቸዉን መድሃኒት ሙሉ በሙሉ ያገኙ ህሙማን ምጣኔ | 10 |
| 4 | የታዘዘላቸዉን ሙሉ የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ያገኙ ህሙማን ምጣኔ | 8 |
| 5 | የታዘዘላቸዉን ሙሉ ኢሜጂንግ አገልግሎት ያገኙ ህሙማን ምጣኔ | 7 |
| 6 | የካርድ አወጣጥ አገልግሎት (ቅልጥፍና፣ፍትሀዊነት፣ካርድ መጥፋት) | 5 |
| | **አገልግሎት አሰጣጥ አመላካቾች (Service Delivery)** | 18 |
| 7 | በ5 ደቂቃ ትሪያጅ የተደረጉ የድንገተኛ ህክምና ተጠቃሚዎች ምጣኔ | 3 |
| 8 | በ24 ሰዓት ዉስጥ ከድንገተኛ ህክምና ክፍል ታክመዉ የወጡ ህሙማን ምጣኔ | 2 |
| 9 | ረዥሙ የቀዶ ጥገና ህክምና የቆይታ ጊዜ (ከአንድ ወር በታች (6 ነጥብ)፣ ከ1-3 ወር (3 ነጥብ) ፣ ከ3-6 ወር (1)፣ ከ6 ወር በላይ (0 ነጥብ)) ይሰጠዋል፡፡ መረጃ ከላይዝን ይገኛል፡፡ | 6 |
| 10 | ከ2፡30 አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ተመላለሽ የህክምና ክፍሎች | 3 |

| | | |
|---|---|---|
| 11 | በስታንዳርዱ መሰረት የተሰጠ የነርሲንግ አገልግሎት | 4 |
| | **የጤና አሰራር ስርዓት አመላካቾች** | **32** |
| 12 | በተቋሙ የመድኃኒት መዘርዝር መሰረት የመሰረታዊ የበጀት መድሃኒቶች አቅርቦት ምጣኔ | 7 |
| 13 | በጤና ጥበቃ ከሚጠበቀው 85 የላብ ምርመራ አገልግሎት በመሰራት ላይ ያለ ሽፋን | 8 |
| 14 | የባለሙያ እርካታ ምጣኔ (staff satisfaction) | 3 |
| 15 | የበጀት አጠቃቀም ምጣኔ (Rate of budget utilization) | 2 |
| 16 | በወቅቱና በቀረበው እስፔስፊኬሽን ይቀርባል ወይ | 3 |
| 17 | ውጤታማ የአፈጻጸም ግምገማ ቡድን (Performance Review Team) መኖር (ቃለ ጉባኤ አለ ፣ HMIS ላይ ይወያያል ፣በመረጃ ላይ ተመስርቶ አፈጻጸም ይገመግማል ፣ዝርዝር የትግበራ ዕቅድ ያዘጋጃል ፣ ግብረመልስ በጽሁፍ ለስራ ክፍሎች ይሰጣል ወይ// | 3 |
| 18 | ከተገልጋይ ቀርበዉ የተፈቱ ቅሬታዎች ምጣኔ | 3 |
| 19 | ቦርዱና ማኔጅመንቱ የመልካም አስተዳደር እቅዶችን (ውስጥና የውጭ) ቋሚ አጀንዳ አድርገጎ መወያየት | 3 |
| | **አጠቃላይ የመልካም አስተዳደር ጭማቂ ውጤት (GG Index)** | 100 |

## አባሪ 7፡-የቦርድ ሰያሚ አካላት የሥራ አፈጻጸም መመዘኛ ነጥቦች

1. በሆስፒታሎች በመመሪያዉ መሰረት ቦርድ እንዲቋቋም ድጋፍ ያደርጋል፤ ወቅታዊ ምለሽ ይሰጣል ?--------------------

   ----------------------------------------------------------------------------------------------------

2. እቅድ በየደረጃዉ ወቅቱን ጠብቆ እንዲታቀድ እና ወደስራ እንዲገባ ያደርጋል ? --------------------------------------

   ------------------------------------------------------------------------------------------

3. በጤና ክብካቤ ሃብት ማግኛ ሪፎርም ላይ አቅዶ በመስራት ተጨባጭ ለዉጥ ለማምታት ጥረት ያደርጋል ?

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

4. ወቅቱን የጠበቀ የቦርድ አፈጻፀም ሪፖርት እንዲልኩ ያደርጋል ?(ሪፖርት ሳይቆራረጥ ይቀበላል፤ግብረ መላስ ይሰጣል)---

   ----------------------------------------------------------------------------------------------------

5. ስራ አመራር ቦርዱ የሚገጥማቸዉ ተግዳሮትን በጋራ ወይም በተናጥል ለማገዝ የሚያደርግዉ ድጋፍ አለ ? ------------

   ----------------------------------------------------------------------------------------------------

6. የቦርድ አባላት እርሰ በእርስ ና የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ የስራ አፈጻጸም በቅፁ መሰረት የአፈጻፀም ምዘና ዉጤት እንዲልኩ ያደርጋል ?----------------------------------------------------------------------------------------------------

7. የሥራ አመራር ቦርድ የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት የልምድ ልዉዉጥ እንዲያገኙ ያደርጋል ? -------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

8. የስራ አመራር ቦርድ የአቅም ማጎልበቻ ተግባራት ያከናዉናል ?--------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

9. በነባር ሆስፒታሎች ላይ ያለዉን የቦርድ አፈጻጸም እንዲጠናከር ድጋፍ ያደርጋል ? -------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

10. አጠቃላይ የሆስፒታል ቦርድ የስራ የስራ አፈፃፀም የጋራ ግምገማ ያደርጋል፤ የማበረታቻ ፕሮገራም ያከናዉናል ?

**ማጠቃለያ፡-**

የታየ ጠንካራ ጎን፡----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

ወደፊት መስተካከል ያለባቸዉ ጉዳዎች፡----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------